መንፈሳዊ መሪ

ትርጉም:- በተስፋዬ መስፍን

This book is sponsored by OM Publishing
P.O. Box 300, Carlisle, Ocumbria, CA 3, OQS,
U.K.

Spiritual Leadership

By:- J.Oswald Sanders
Translated by:- Tesfaye Mesfin

Grace Christian book Center
P.O. Box 34251
Addis Ababa/ Ethiopia
E-mail: grchbook@yahoo.com

ስለዚህ መጽሐፍ ያለምትን አስተያየት፡-
ጸጋ ክርስቲያን መጽሐፍ መደብር
የመ.ሣ.ቁ. 34251
አዲስ አበባ በማለት ይጻፉልን
1996 ዓ.ም

መቅድም

መጠኑ ይብዛ ይነስ እንጂ እያንዳንዳችን መሪዎች ነን ማለት ይቻላል። የቤተሰብ መሪዎች ልንሆን እንችላለን፤በተለያየ የሥራ መስክ ኃላፊነት ያለብን ሰዎች ልንሆን እንችላለን። በዚህም ሆነ በዚያ በመጽሐፉ የተካተቱ ባሕርያትን አሟልቶ መገኘት በተሰማራንበት ቦታ ሁሉ ለውጤታማነት እንደሚያበቃ የብዙዎች እምነት ነው።

መጋቢዎች(ፓስተሮች)፥ወንጌላውያን፥የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች፥በተለያዩ ክርስቲያናዊ ድርጅት በኃላፊነት ወይም በሌላ ሥራ የተሰማሩ ወገኖች ከዚህ መጽሐፍ የሚያገኙት ቅርስ ከቶውንም በዋጋ ሊተመን የሚችል አይደለም።

ይህ መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ የተዘጋጀው ከብዙ ዓመታት በፊት ቢሆንም ጠቃሚነቱ ስለታመነበት በተደጋጋሚ ታትሞአል፤በአያሌ ቋንቋዎች ተተርጉሞአል። የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጆች፥ሰሚናሪዎች፥ክርስቲያናዊ የሥልጠና ተቋማት መሪነትን በተመለከተ አሁንም ቢሆን ለማስተማሪያነት የሚጠቀሙት በዚህ መጽሐፍ ነው። ዛሬ ደግሞ የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ በዚህ መልኩ ለአማርኛ አንባቢዎች ቀርቦአል።

መጽሐፉ በሀገራችን ሲታተም ይህ የመጀመሪያ አይደለም፤ከብዙ ዓመታት በፊት በኤስአይኤም አሳታሚነት "ለታማኝ አገልጋይነት የሚጠቅሙ ባሕርያት" በሚል ርዕስ ቀርቦ ብዙዎችን ሲባርክ መኖሩ ይታወሳል። ይሁን እንጂ መጽሐፉን በእንግሊዝኛ ያዘጋጀው ድርጅት እንደገና እንዲተረጎም ባቀረበው ሀሳብ መሠረት በዚህ መልኩ ቀርቦአል። ይህን መጽሐፍ ስተረጉም ቀደም ሲል በአማርኛ ቀርቦ የነበረው እገዛ አድርጎልኛል።

ተርጓሚው

መታሰቢያ

የተከበሩ በጌታ ወንድማችን፡- ሚስተር ጄራልድ ጐትዘን፤

ካለፉት ሰላሣ ስምንት ዓመታት ጀምሮ ክርስቲያናዊ መጻሕፍትን በማሳተም፣ ችግር ላይ የነበሩ አብያተ ክርስቲያናትን በተለያየ መልኩ በማገዝ፣ አገራችን የእምነት ነፃነትን በተነፈገችበት የኮሚኒዝም ሥርዓት ዘመን ያዘኑና የተጎዱ ክርስቲያኖችን በማጽናናት ከሁሉም በላይ ደግሞ ምሳሌነት ያለው ሕይወትዎን እኛ በቅርብ የምናውቅዎት ሁሉ የምንመሰክረው ነው። የክርስቲያን አገልጋይ ትልቁ ናፍቆትና ተስፋ "አንተ ታማኝ ባሪያ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ" የሚለውን አምላካዊ ቃል መስማት እንደሆነ እንገነዘባለን። ያም ሆኖ ለመልካም ሥራዎ ባይመጥን እንኳን ይህን "መንፈሳዊ መሪ" የተሰኘ መጽሐፍ ለመታሰቢያዎ ስናበረክት በቃላቅ ደስታ ነው።

ኢትዮጵያውያን ወዳጆችዎ

Dedication

To Our dear brother in the Lord Gerald Gotzen.

We acknowledge your excellent work for the past 38 years by sponsoring the production of Christian literature helping churches in their times of need. We were very thankful for all your comfort and encouragement during the years of communist government when many churches were closed. Above all we appreciate your exemplary Christian life which we have watched as you lived among us.

We know that love for the Lord Jesus Christ is the motivation of your service.We recognize that the greatest hope and desire of a Christian leader is to hear the voice of the master saying "Well done, good and faithful servant enter into the joy of thy Lord" We are sure that this will be said of you dear brother. The dedication of this book cannot convey our enormous appreciation for all that you have done for us. However it is with great joy and respect that we dedicate this book "spiritual leadership" to you.

Your Ethiopian Friends.

ማውጫ

ምዕራፍ ገጽ

1. መልካም ምኞት 1
2. ተፈላጊ መሪ 5
3. ዐቢይ አምላካዊ መርሖ 9
4. የተፈጥሮ ችሎታና መንፈሳዊ መሪነት 15
5. እምቅ የመሪነት ችሎታን እንዴት ማወቅ እንደሚቻል 23
6. መሪነትን በተመለከተ ጳውሎስ የሰጠው መመሪያ 28
7. መሪነትን በተመለከተ ጴጥሮስ ያቀረበው መመሪያ 38
8. ለመንፈሳዊ መሪ የሚያስፈልጉ ባሕርያት 1 43
9. ለመንፈሳዊ መሪ የሚያስፈልጉ ባሕርያት 2 58
10. እጅግ አስፈላጊው ነገር 72
11. መንፈሳዊ መሪውና የጸሎት ሕይወቱ 78
12. መንፈሳዊ መሪውና የጊዜ አጠቃቀሙ 89
13. መንፈሳዊ መሪውና የማንበብ ልምዱ 97
14. የመሪነት አቅምን ማዳበር 106
15. መንፈሳዊ መሪነት የሚያስከፍለው ዋጋ 112
16. የመንፈሳዊ መሪ ኃላፊነቶች 121
17. መንፈሳዊ መሪነት ሊፈተን 127
18. አገልግሎትን ለሌሎች የማካፈል ጥበብ 134
19. መሪዎችን ስለመተካት 139
20. ተተኪ አገልጋዮችን ስለማፍራት፣ ስለማሰልጠን 144
21. መንፈሳዊ መሪው ሊገጥሙት የሚችሉ አንዳንድ ፈተናዎች 149
22. ነህምያ፡- በምሳሌነት የሚጠቀስ መሪ 161

1

መልካም ምኞት

ማንም ኤጲስ ቆጶስነትን (መሪነትን) ቢፈልግ መልካም ሥራ ይመኛል
1ኛ ጢሞቴዎስ 3:1

ለራስህ ታላቅን ነገር ትፈልጋለህን? አትፈልገው
ኤርምያስ 45:5

ብዙ ክርስቲያኖች መሪነትን መመኘት ትክክለኛ መሆኑን መቀበል ይከብዳቸዋል። ስለሆነም «አንድ ሰው የመሪነትን ቦታ መመኘት አለበት ወይስ ቦታው ራሱ ሰውየውን ሊፈልገው ይገባል? ሹመትን ወይም ሥልጣንን መመኘት አደገኛ ነገር ሊሆን አይችልም?» በማለት ይጠይቃሉ። ሼክስፒር የተባለ ባለቅኔ፦

> እባክህን ምኞትን አውጣና ጣለው፤ መላእክት ከደረጃቸው የወደቁት በዚያ ኃጢአት ምክንያት ነው። ታዲያ መላእክትን እንኳ ካዋረደ የሰው ልጅንማ እንዴት ሊጠቅመው ይችላል? ማለቱም ይጠቀሳል።

ከአንዳንድ አንገብ ምኞት አኳያ ስንመለከተው እነዚህ አባባሎች ትክክል ሊሆኑ ይችላሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ተገቢና ሊበረታታ የሚገባው ምኞት ሊኖር እንደሚችል ግልጽ ነው። ፍሬያማ በሆነ ሁኔታ እግዚአብሔርን ማገልገል የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ከእርሱ የተቀበላቸውን አቅምና ችሎታዎች ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ ተግባር ላይ ቢያውላቸው ችግር ላይ እወድቃለሁ ብሎ መፍራት አይኖርበትም።

መሪ መሆንን ስለ መፈለግ ጳውሎስ የሰጠውን አሳብ እውን በማድረግ ረገድ አንዳንድ መሠረታዊ ነጥቦችን ማስተዋል ተገቢ ነው። ስለ መሪዎች ስናስብ ቶሎ ትዝ የሚለን በእሁን ዘመን ያሉ ክርስቲያን መሪዎች ያላቸው ክብርና ሥልጣን ነው። ጳውሎስ ይህን በጻፈበት ዘመን ግን ሁኔታዎች የተለየ መልክ ነበራቸው። በዚያ ዘመን ክርስቲያን መሪ መሆን ከባድ ኃላፊነት ያለበትና ለተለያየ አደጋ የሚያጋልጥ ስለ ነበር ማንም ተነሥቶ የሚመኘው አልነበረም። ክርስቲያን መሪ መሆን ማለት ለችግር፣ ለመከራ፣ ለመናቅና በማጎበረ ሰቡ ለመገለል ራስን ማጋለጥ ማለት ነበር። ስደት ቢነሣ መጀመሪያው ተጠቂ መሪው ራሱ ነበር የሚሆነው።

እንግዲህ ይህን ግምት ውስጥ በማስገባት የጳውሎስን ቃል ስንመለከት መሪነት ማንም ሰው የሚመኘው ወይም የሚጓጓለት ሊሆን እንደማይችል ግልጽ ነው። ጀብደኞችና ሥልጣን ናፋቂዎች የሚፈልጉት ሊሆን አይችልም። ቤተ ክርስቲያን ይህን በመሰለ ሁኔታ በነበረችበት ወቅት መሪ መሆን ለሚፈልጉ ሰዎች ጳውሎስ የሚያበረታታ ቃል መናገሩ ተገቢ ስለነበር «ማንም ኤጲስ ቆጳስነትን (መሪነትን) ቢፈልግ መልካም ሥራ ይመኛል» አለ።

በአንዳንድ አገሮች ዛሬም ቢሆን ክርስቲያን መሪ መሆን ለአደጋ የሚያጋልጥ እንጂ ክብርና ጥቅም የሚያስገኝ አይደለም። ለምሳሌ ቻይናን የወሰድን እንደሆነ በግንባር ቀደም ደረጃ በኮሚኒስቶች ከባድ መከራና ስደት የደረሰባቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደነበሩ ይታወቃል። በኔፓልም እንዲሁ እስር ላይ የነበሩ ክርስቲያኖችን ከፈተ በኋላ የቤተ ክርስቲያን መጋቢው ግን ለዓመታት እንዲታሰር ተፈርዶበታል። መንፈሳዊ መሪ መሆን ዛሬም ቢሆን በብዙ አገሮች ክብር የሚያስገኝ ነገር አይደለም።

እዚህ ላይ ጳውሎስ መሪነትን መመኘት መልካም እንደሆነ ቢናገርም ዋናው ትኩረቱ ሥራው ላይ እንጂ ሥልጣኑ ላይ አልነበረም። መልካም ሥራ ወይም ምኞት የሚለው ሥልጣኑን ሳይሆን ተግባሩን ነው። በዚህ ዓለም ካሉ የሥራ ዓይነቶች ይልቅ መሪ መሆን ትልቅ መታደል በመሆኑ በቅን ልቦና ተነሣሥተን ከፈለግነው ለአሁኑም ለዘላለም ክብርን የሚያስገኝ ነው። ጳውሎስ በነበረበት ዘመን መሪ መሆንን የሚመኙ ለክርስቶስ ጥልቅ ፍቅር ያላቸውና የቤተ ክርስቲያንም ሁኔታ የሚያሳስባቸው ሰዎች ብቻ ነበሩ። በዚህ ዘመን ግን ከአንዳንድ ሁኔታ ማየት እንደሚቻለው ክርስቲያን መሪ መሆ ማለት ክብርና ሥልጣንን የማግኛ መንገድ ሆኖአል፤ አንዳንድ ጊዜም መንፈሳዊነት የሌላቸው ሰዎች ስፍራውን ሲይዙ ይታያል።

«ለራስህ ታላቅን ነገር ትፈልጋለህን? አትፈልገው» በማለት ነቢዩ ኤርምያስ ባሮክን የሚመክረውም ይህን ግምት ውስጥ በማስገባት ነበር። እዚህ ላይ «አትፈልገው» ሲል መልካም ነገርን መፈለግ በራሱ መጥፎ ነው ማለቱ ሳይሆን፣ ክብርና ዝናን እንዲሁም ጥቅማ ጥቅም መሠረት በማድረግ መጓጓት እንደሌለበት ለማስገንዘብ ነበር። ትልቅ ለመሆን መመኘት በራሱ ኃጢአት አይደለም። ኃጢአት የሚያደርገው የራስን ስግብግብ ምኞት ለማሳካት ሲባል ትልቅ መሆንን ስንፈልግ ነው። ጌታ የሚያወግዘው ትልቅ ለመሆን ያለንን ምኞት ሳይሆን የተሳሳተ ዓላማን ነው። ከተሳሳተ ዓላማ ተነሥተን ትልቅ መሆን መመኘት የለብንም።

ክርስቲያኖች ሁሉ እግዚአብሔር የሰጣቸውን አቅምና ችሎታ የማዳበርና ጥቅም ላይ የማዋል ኃላፊነት አለባቸው። ያም ሆኖ ግን የራስን ስግብግብ ዓላማ ለማሳካት ትልቅ ነገርን መመኘት ትክክል እንዳልሆነ ጌታ ኢየሱስ አስተምሮአል። አገልጋዮችን ለመሾም በተደረገ ስብሰባ አንድ ሰው ሲናገሩ «ተራ በሆነ መልኩ ስንመለከተው ምኞት ምንጊዜም ኃጢአት ነው። በተለይም ደግሞ እግዚአብሔርን ለማገልገል ውሳኔ ያደረገ ሰው ትልቅ መሆንን ሊመኝ ኃጢአቱን እጥፍ ድርብ ያደርገዋል» ብለው ነበር። በሌላ መልኩ ስንመለከተው ደግሞ ለእግዚአብሔር ክብርና ለቤተ ክርስቲያን በጎነት እስከሆነ ድረስ ትልቅ ነገርን ቢመኝ ተገቢ ከመሆኑም በላይ ሊበረታታ የሚገባው ነው ማለት ነው።

«ምኞት» የሚለውን ቃል በላቲንኛ ትርጉሙ ስንመለከተው «አንድ ሰው ራሱን ከፍ ከፍ ለማድረግ የሚኖረው መንጠራራት ወይም መፍጨርጨር» የሚል ሃሳብን ያዘለ ነው። ምኞት የተለያየ መልክና ገጽታ አለው። በሰዎች ለመታየትና ለመመስገን፣ ታዋቂና ተወዳጅ ለመሆን፣ ከጓደኞቻችን ይልቅ ደምቀን ለመታየት ወይም ደግሞ በሌሎች ላይ የበላይ ለመሆን የምናደርገው ሙከራ ሁሉ «ምኞት» በሚለው ቃል ይጠቃለላል። በእንዲህ ባለው ምኞት የሰከሩ ሰዎች ገንዘብ ወይም ሥልጣን የሚያስገኘውን ክብር አጥብቀው ይፈልጉታል። እንዲህ ያለውን ሥጋዊ ምኞት ጌታ በጥብቅ አውግዞአል። እውነተኛ መንፈሳዊ መሪ ልቆና ደምቆ ለመታየት አጉል አይንጠራራም።

አብረዋቸው ከነበሩት ይልቅ ከፍ ብለው የመታየት ፍላጎት ለነበራቸው ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ትልቅነትን በተመለከተ አዲስ መመሪያ ሰጥቶአቸዋል፦ «የአሕዛብ አለቆች ተብለው የሚታሰቡት እንደሚገዟቸው ሹሞቻቸውም በእነርሱ ላይ ሥልጣናቸውን እንደሚያሳዩ ታውቃላችሁ፤ በእናንተ ዘንድ ግን እንዲህ አይደለም፤ ከመካከላችሁ ታላቅ መሆን የሚፈልግ ሁሉ አገልጋይ ይሁን፤ ፊተኛ ለመሆን የሚፈልግ ሁሉ፤ የሁሉ ባሪያ ይሁን» (ማር. 10:42 - 44 አ.መ.ት) ኢየሱስ ይህን የተናገረው ከምን ተነሥቶ እንደነበር በሌላው ምዕራፍ በስፋት የምንመለከተው ይሆናል። ስለ መንፈሳዊ መሪነት ስናጠና ማስተዋል ያለብን አንድ መሠረታዊ መርሖ አለ። ይኸውም እውነተኛ ትልቅነት፣ እውነተኛ መሪነት፣ ሌሎች እንዲያገለግሉን ሳይሆን ሌሎችን ለማገልገል ያለምንም ስስት ራሳችንን መስጠት መሆኑን ነው። ይህ ደግሞ ዋጋ ያስከፍላል። መራራውን ጽዋ መጠጣትና በመከራ መጠመቅን ይጠይቃል። አንድ እውነተኛ መንፈሳዊ መሪን ይበልጥ የሚያላስበው እግዚአብሔርንና ሰዎችን

ማገልገል እንጂ ከሁኔታዎች የሚያገኘው ጥቅም አይደለም። ዓለማው መስጠት እንጂ መቀበል አይሆንም።

«በመጨረሻው ፍርድ ይፋ የሚወጣ ነገር ቢኖር የሰዎች ሥራ እንጂ የነበራቸው ሥልጣን ትልቅነት አይደለም፤ የልባቸው ዝንባሌና ባሕርያቸው እንጂ ደረጃቸው አይደለም» በማለት የተናገረው ብሬንግል የተባለ ሰው ነበር።

«የአንድ ሰው ምኞት እግዚአብሔር ለሕይወቱ ላለው እቅድ የተመቸ ሆኖ መገኘት እስከሆነ ድረስ በማዕበል በሚናወጥ ባሕር ውስጥ ቢያልፍ እንኳ የሰሜን ኮከብን ያህል የሚመራው ዓላማ ይኖረዋል።» በማለት የጻፈው ደግሞ ኤስ. ዲ ጐርደን መሆኑ ይጠቀሳል።

አንድ ሌላ ሰው ደግሞ ስለ ሕይወት ዓላማውና ምኞቱ ሲናገር፣ «አንድ ከፍተኛ ምኞትና ዓላማ አለኝ፤ ይኸውም፦ እርሱና እርሱን ብቻ ነው» ብሎአል። ይህን ሰው ራስ ወዳድነትና ስግብግብነት ላይ የተመሠረተ የራሱን ሕይወት እርግፍ አድርጐ በመተው የአንድ ታላቅ ክርስቲያናዊ እንቅስቃሴ መሥራችና መሪ ለመሆን በቅቶአል። ዓላማና ምሳሌነቱን መመሪያ ያደረጉ ተከታዮቹም ዓለምን በወንጌል ለመድረስ ታላቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ይህንኑ ተልዕኮ እውን ለማድረግ ከተከታዮቹ ብዙዎቹ ወደ ተለያዩ አገሮች ተሰማርተዋል።

2

ተፈላጊ መሪ

ክብር ከምሥራቅ ወይም ከምዕራብ ወይም ከምድረ በዳ የለምና
እግዚአብሔር ፈራጅ ነውና ይህን ያዋርዳል ይህንም ያከብራል
መዝሙር 75:6-7::

እግዚአብሔርም ሆነ ሰዎች ለተለያዩ ክርስቲያናዊ አገልግሎት ዘርፎች እውነተኛ መሪዎችን እየፈለጉ ነው:: እግዚአብሔር የራሱ የሆነ ሰውን መፈለጉ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተደጋጋሚ ተጠቅሶአል:: ብዙዎችን ሳይሆን አንድ ሰው፣ ቡድንን ሳይሆን ለእርሱ የተሰጠ ግለ ሰብን ይፈልጋል:: «እነሆ እግዚአብሔር እንደ ልቡ የሚሆንለትን ሰው አግኝቶአል» (1ኛ ሳሙ. 13:14 አ.መ.ት)::

«አየሁ፤ እነሆም ሰው አልነበረም» (ኤር. 4:25)::

«በኢየሩሳሌም መንገድ እየተመላለሳችሁ ሩጡ፤ ተመልከቱም፤ እወቁም፤ በአደባባይዋም ፈልጉ፤ ፍርድን የሚያደርገውን እውነትንም የሚሻውን ሰው ታገኙ እንደሆነ ይቅር እላታለሁ» (ኤር. 5:1)::

«ቅጥርን የሚጠግን፤ ምድሪቱንም እንዳላጠፋት በፈረሰበት በኩል በፊቴ የሚቆምላትን ሰው በመካከላቸው ፈለግሁ፤ ነገር ግን አላገኘሁም» (ሕዝ. 22:30)::

እርሱ የሚፈልገውን መንፈሳዊ መስፈርት የሚያሟላና የሚጠበቅበትን ዋጋ ለመክፍል ዝግጁ የሆነ ሰው ቢገኝ፣ በሌላ ጐኑ ደካማና ጉዶሎ ቢሆን እንኳ እግዚአብሔር በአስደናቂ ሁኔታ እንደሚጠቀምበት ከቅዱሳት መጻሕፍትና ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ መመልከት ይቻላል:: እግዚአብሔር ከተጠቀመባቸው እንዲህ ያሉ ሰዎች መካከል ሙሴን፣ ጌዶዎንን፣ ዳዊትን፣ ማርቲን ሉተርን፣ ጆን ዌስሊንና ሌሎች ብዙዎችን እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል::

የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ መለኮታዊ እንደመሆኑ መጠን ከሰብዓዊ ግምትና አስተሳሰብ የላቁ መሪዎች ያስፈልጉአታል:: ታዲያ፣ አንዲህ ያለውን መስፈርት የሚያሟሉ ሰዎችን እንዴት ወይም ከየት ማግኘት ይቻላል? በአንድ መልኩ ስንመለከተው ኃላፊነቱ ከባድ ወይም ታላቅ ከመሆኑ የተነሣ እንዲህ ያሉ ሰዎችን በብዛት ማግኘት እንደማይቻል ግልጽ ነው::

አንድ ሰው ሲናገር «ቤተ ክርስቲያን መሪዎችን በጥብቅ እየፈለገች ነው። ሆኖም፣ «እኔ አለሁ!» የሚል የአንድ ሰው ምላሽ እንኳ ማግኘት አልተቻለም። በየኮንፈረንሱና በቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎች ራቅ ያሉ ወንበሮች ላይ መቀመጥ እንወዳለን። ከመናገር ይልቅ መስማትን መርጠናል፤ በጣም የሚገርመው ግን ለጥሪው ምላሽ የሚሰጥ ሰው ድምፅ መስማት አልቻልንም» ብሏል።

ቤተ ክርስቲያን ግዴታዋንና ኃላፊነትዋን ለተተኪው ትውልድ ማስተላለፍ እንድትችል በሥልጣን፣ በእውነተኛ መንፈሳዊነትና መሥዋዕትነት የሚያገለግሉ መሪዎች በጥብቅ ያስፈልጉአታል። በሥልጣን የሚያገለግሉ መሪዎች የሚያስፈልጉበት ምክንያት ሰዎች ወዴት እንደሚሄድ የሚያውቅና ለመንፈሳዊ ነገር ምሪት መስጠት በሚችል መሪ መመራትን ስለሚወዱ ነው። በሚያምነው መሠረት የሚኖረውን አስተዋይና ብርቱ መሪ ሰዎች ያለ አንዳች ማወላወል ይከተላሉ። አንዳንድ ሰዎች በተፈጥሮ የታደሉት ስጦታ ሊኖራቸው ይችላል፤ ሰዎችን የሚማርክ ዕውቀትና ብቃትም ሊኖራቸው ይችላል፤ መንፈሳዊነት ከሌላቸው ግን ውጤቱ ሞራላዊና መንፈሳዊ ባዶነት ይሆናል። ከመሪዎች መንፈሳዊነት የሚጠበቀውም ይህ እንዳይሆን ነው። ለዓለም ሕዝብ ሁሉ መሥዋዕት ለመሆን ክርስቶስ ራሱን ሰጥቶአል፤ ምሳሌውን እንድንከተልም ፍለጋውን ትቶልናል። የክርስቶስን ምሳሌነት የሚከተል መሪን ደግሞ ሰዎች ደስ እያላቸው ይከተሉታል። ከመንፈሳዊው መሪ የዚህ ዓይነቱ መሥዋእትነት የሚጠበቀውም በዚህ ምክንያት ነው።

መንፈሳዊነት ባላቸውና በመለኮታዊ ኃይል በተዳሰሱ አገልጋዮች የምትመራ ቤተ ክርስቲያን ምን ጊዜም ታላላቅ ውጤቶችን ስታስመዘግብ ኖራለች። እንዲህ ያሉ መሪዎችን ማጣት ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ውድቀት ለመቃረቡ ዓይነተኛ ምልክት ነው። ከዚህ ቀደም ከቤተ ክርስቲያን መድረክ ይሰሙ የነበሩ፣ የሰዎችንም ሕይወት ይለውጡ የነበሩ አገልጋዮች ድምፅ በአሁን ጊዜ የሚሰማው በጣም በጥቂቱ ነው። ዓለም በችግርና በመከራ ባለችበት በዚህ ዘመን የቤተ ክርስቲያን ድምፅ የሽክሽክታ ያህል ብቻ ነው እየተሰማ ያለው። ተጨባጩን ሐቅ ተገንዝበው የወንጌልን ችቦ ለወጣቱ ትውልድ ለማስተላለፍ እውነተኛ መንፈሳዊ መሪዎች የሚቻላቸውን ሁሉ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

ስለ መሪነት ስንናገር ቶሎ ወደ አእምሮአችን የሚመጣው በተፈጥሮ ችሎታ የታደለ፣ ጠንካራ ሰብዕና ያለውና በእውቀቱም ከሌሎች ልቆ የሚገኝ ሰው ነው። በመሠረቱ እንዲህ ያሉ ችሎታዎች አንድን ሰው

ብቁና ለቦታው የሚመጥን እንደሚያደርጉት መካድ አይቻልም፤ መንፈሳዊ መሪነትን በተመለከተ ግን እነዚህ ነገሮች ይህን ያህል ወሳኝ አይደሉም። እውነተኛ አገልጋዮች ላመኑበት ዓላማ መከራ ለመቀበል የቆረጡና በሙሉ ልባቸው ለመታዘዝ የተዘጋጁ ናቸው።

መንፈሳዊ መሪዎች በሰዎች የሚመረጡ፣ በተለያዩ ኮሚቴዎች የሚሾሙ አይደሉም። መሪዎችን የሚያስነሣ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ወሳኝና ቁልፍ ቦታ ላይ መቀመጡ ብቻ አንድን ሰው እውነተኛ መሪ አያደርገውም፤ የተለያዩ ኮርሶችና ሥልጠናዎችን መካፈሉም ለመሪነት አያበቃውም። አንድ ሰው የመሪነት ብቃት የሚኖረው የሚጠበቅበትን መሥፈርት አሟልቶ ሲገኝ ብቻ ነው። የሃይማኖት ተቋማት ካህናትን መሾም ይችላሉ፤ መንፈሳዊ ሥልጣንን መስጠት ግን አይችሉም፤ ለክርስቲያን መሪ በጣም አስፈላጊው ነገር ደግሞ መንፈሳዊ ሥልጣን ነው። ብዙውን ጊዜ መንፈሳዊ ሥልጣን የሚመጣው ፈልገውት ሳይሆን ሳይፈልጉት ነው፤ እንዲህ ያሉ ሰዎች ገና በወጣትነት ዘመናቸው በመንፈሳዊነት፣ ራስን በመግዛትና የክርስትና ሕይወታቸውን በማሳደግ ብቃታቸውን አሳይተዋል። «ለራስህ ታላቅን ነገር ትፈልጋለህን? አትፈልገው» የሚለውን ምክር ተግባራዊ በማድረግም ከራሳቸው ይልቅ የእግዚአብሔርን መንግሥት አስቀድመዋል። መንፈሳዊ መሪነት የመንፈስ ቅዱስ ጉዳይ ነው፤ ያንን መስጠት የሚቻለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ሁሉን መመርመር የሚችል የእግዚአብሔር ዓይን መስፈርቱን አሟልቶ በተገኘ ሰው ላይ ሲያርፍ፣ ያንን ሰው በመንፈሱ ይቀባዋል፤ ለራሱ አገልግሎትም ይለየዋል (የሐዋ. 9፡17፣ 22፡21)።

ሳሙኤል ሎጋን ብሬንግል በአንድ እውቅ ክርስቲያናዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ቁልፍ የመሪነት ስፍራ ነበረው። ይህ ሰው በጣም መንፈሳዊ ከመሆኑም በላይ በእውቀቱም አንቱ የተሰኘ ነበር። መንፈሳዊ ሥልጣንና መሪነትን አስመልክቶም የሚከተሉትን ድንቅ ቃላት ተናግሮአል፦

> ቤተ ክርስቲያን በምትሰጠው እድገት ሳይሆን በብዙ እንባና ጸሎት የሚገኝ ነው። ልብን በመመርመር፣ ራስን አሳልፎ በመስጠትና በእግዚአብሔር ፊት ትሑት ሆኖ በመቅረብ፣ ያለምንም ማንጐራጐር ዕለት ዕለት መስቀሉን ተሸክሞ በመኖርና የተሰቀለው ክርስቶስን ትኩር ብሎ በመመልከት የሚገኝ ነው። ለራሳችን ታላቅ ነገርን በመፈለግ ሳይሆን፣ ጳውሎስ እንዳደረገው ጥቅም ያለበትን ነገር ስለ ክርስቶስ ስንል እንደ ጉዳት በመቁጠር

ነው። እርግጥ ነው የሚያስከፍለው ዋጋ ከባድ ነው፤ ይሁን እንጂ እውነተኛ መንፈሳዊ መሪ መሆን የሚፈልግ ሁሉ ይህን ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ መሆን ይኖርበታል።

እግዚአብሔር የሚፈልገው እንዲህ ዓይነቱን ሰው ነው፤ ኃይልና ብርታቱን የሚገልጠውም በእንዲህ ባለው ሰው በኩል ነው (2ኛ ዜና 16:9)። ሆኖም የመሪነትን ሥልጣን የሚመኙ ሁሉ ተገቢውን ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኛ ናቸው ማለት አይቻልም። ይሁን እንጂ፣ ፈቃደኛ የሆነውን ሰው እግዚአብሔር በግልጽ በአደባባይ ከማክበሩ በፊት ተገቢውን ዋጋ በስውር እንዲከፍል ይጠይቀዋል። በእርሱ መንግሥት ውስጥ መሪ የመሆኑ ጉዳይ የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ምርጫ እንጂ የሰዎች ማንነት ውጤት እንዳልሆነ ጌታ ለያዕቆብና ለዮሐንስ ግልጽ አድርጐላቸዋል። በእግዚአብሔር መንግሥት ከፍተኛውን ስፍራ የሚይዙት ማንም ሳያውቅ በስውር ራሳቸውን ያዘጋጁና ብቁ ሆነው የተገኙ ናቸው። ቀድሞውኑ በእግዚአብሔር ሉዓላዊነት የተመረጡ በመሆናቸው በአደራ ለተቀበሉት ኃላፊነት ብቁ እንዲሆኑ በፍርሃትና በትሕትና የሚኖሩት ከዚህ የተነሣ ነው።

የመሪነት ሥልጣንን ለተሳሳተ ዓላማ መጠቀም እንደሚቻል ግልጽ ነው። መሪዎች ሕዝቡን ወደ ላቀ መንፈሳዊ ደረጃ ማድረስ ካልቻሉ ውጤቱ የተገላቢጦሽ ይሆንና ተያይዘው ቁልቁል ይወርዳሉ፤ ምክንያቱም ማንም ለራሱ የሚኖር የለምና፤ ውድቀታችንም ሆነ ስኬታችን ለሌላውም ይተርፋል።

3

ዐቢይ አምላካዊ መርሖ

ከመካከላችሁ ታላቅ መሆን የሚፈልግ ሁሉ አገልጋይ ይሁን፤ ፊተኛ ለመሆን የሚፈልግ ሁሉ፣ የሁሉ ባሪያ ይሁን
ማርቆስ 10:43-44 አ.መ.ት::

ዓለማዊም ሆኑ መንፈሳዊ መሪዎች ያለባቸው ኃላፊነት ከባድ ከመሆኑ አንጻር መጽሐፍ ቅዱስ መሪ በሚለው ቃል የተጠቀመው ስድስት ጊዜ ብቻ መሆኑ በጣም የሚገርም ነው፤ ሦስት ጊዜ በነጠላ ቍጥር ሲጠቀም፣ ሦስት ጊዜ ደግሞ መሪዎች በሚለው ብዙ ቍጥር ተጠቅሞአል:: እንዲህ የሆነው መሪነት ዐቢይ ርዕሰ ጉዳይ ሳልልሆነ ሳይሆን፣ ይልቁንም መሪ ወይም መሪዎች በሚለው ቃል ምትክ ባሪያ ወይም አገልጋይ በሚለው ቃል በመጠቀሙ ነው:: ለምሳሌ ያህል «ባሪያዬ ሙሴ» ይላል እንጂ «እኔ የመረጥሁት መሪ ሙሴ» አይልም:: ይህም መሪነትን በተመለከተ ክርስቶስ ካስተማረው ጋር ይስማማል::

ምንም እንኳ ፖለቲካዊ በሆነ መልኩ ኢየሱስ ሥር ነቀል ለውጥ አምጪ ነበር ባይባልም መሪዎችን በተመለከተ ያስተማረው ግን ምን ያህል ከዘመኑ አስተሳሰብ የተለየ መሆኑን መመልከት ይቻላል:: አገልጋይ ወይም ባሪያ የሚለው ቃል በዚህ ዘመን ዝቅተኛ ግምት ያለው ቢሆንም ኢየሱስ የተጠቀመበት ግን በዚህ መልኩ አልነበረም:: እንዲያውም ባሪያ ወይም አገልጋይ የሚለውን ቃል የተጠቀመበት ከትልቅነት ጋር በተያያዘ ሁኔታ ነበር፤ ይህም ከዘመኑ አመለካከት ምን ያህል የተለየ እንደሆነ ግልጽ ነው :: ባሪያ ወይም አገልጋይ መሆን ለብዙዎቻችን የማስማማ አይደለም::

ክርስቶስ የመሠረተው መንግሥት አንዱ ሌላውን የሚያገለግልበት ማኅበረሰብ እንጂ አንዱ በሌላው ላይ ጌታ የሚሆንበት አልነበረም:: ጳውሎስም ከዚህ አሳብ ጋር መስማማቱን ሲገልጽ «በፍቅር እርስ በርሳችሁ እንደ ባሪያዎች ሁኑ» አለ (ገላ. 5:13):: ከፍቅር የተነሣ ለሰዎችን እንደ ባሪያ ማገልገል አለብን:: በአሁኑ ዘመን ግን በዚህ መልኩ የሚያገለግሉ መሪዎች እጅግ በጣም ጥቂቶች ናቸው::

ከማገልገል ይልቅ መገልገልን በሚፈልግ ዓለም እርሱ ያስተማረው ትምህርት ተቀባይነት እንደማይኖረው ኢየሱስ በሚገባ ያውቃል::

ይሁን እንጂ ሰዎች ተቀበሉትም አልተቀበሉትም በእርሱ መንግሥት ውስጥ መሪ መሆን የሚፈልጉ ሁሉ ይህን መስፈርት አሟልቶ መገኘት ይጠበቅባቸዋል::

መሪነትን ከተመለከተ ዓለም በሚከተለው መመሪያና በክርስቶስ ትምህርት መካከል ያለው ልዩነት በማርቆስ 10:42-43 በንጽጽር ቀርቦአል:: የአሕዛብ አለቆች ተብለው የሚታሰቡት እንደሚገዟቸው ሹሞቻቸውም በእነርሱ ላይ ሥልጣናቸውን እንደሚያሳዩ ታውቃላችሁ:: በእናንተ ዘንድ ግን እንዲህ አይደለም፤ ከመካከላችሁ ታላቅ መሆን የሚፈልግ ሁሉ አገልጋይ ይሁን፣ ፈተኛ ለመሆን የሚፈልግ ሁሉ፤ የሁሉ ባሪያ ይሁን» (አ.መ.ት)

ይህን ግን ያዕቆብና ዮሐንስ በሚገባ አልተረዱም ነበር:: በእነርሱ አእምሮ ውስጥ የነበረው «እውነት እላችኋለሁ እናንተስ የተከተላችሁኝ በዳግመኛ ልደት የሰው ልጅ በክብሩ ዙፋን በሚቀመጥበት ጊዜ እናንተ ደግሞ በአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ስትፈርዱ በአሥራ ሁለቱ ዙፋን ትቀመጣላችሁ» የሚለው የተስፋ ቃል ነበር (ማቴ. 19:28):: ከስግብግብ ምኞታቸው የተነሣ በሚመጣው መንግሥት ውስጥ ከፍተኛ ውን ስፍራ ለመያዝ ደካማ እናታቸውን አማላጅነት ይዘው የመጡበት ጊዜም ነበር::

ኢየሱስ ግን በዚህ አልተስማማም:: መንፈሳዊ መሪነት በአማላጅ ወይም በዝምድና የሚገኝ አይደለም:: ስለሆነም «የምትለምኑትን አታውቁም» በማለት መለሰላቸው:: የፈለጉት ክብርን እንጂ ለእርሱ ውርደት መቀበልን አልነበረም፤ አክሊልን ወይም ዘውድን እንጂ መስቀልን አልነበረም፤ ጌቶች እንጂ ባሪያ ወይም አገልጋይ መሆንን አልነበረም:: የከበሬታ ስፍራ ለማግኘት ያቀረቡትን ልመና ምክንያት በማድረግ ኢየሱስ ስለ መሪነት ለምን ጊዜም የሚያገለግሉ ሁለት ዋና ዋና መመሪያዎችን ሰጥቶአል::

- *መንፈሳዊ መሪነት በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ምርጫ ላይ የተመሠረተ ነው::*

«በቀኝና በግራ መቀመጥ ግን ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ እኔ የምሰጥ አይደለሁም አላቸው» (ማር. 10:40)::

እኛ ብንሆን ኖሮ ትኩረት የምንሰጠው «መንፈሳዊ መሪነት ለዚሁ ጉዳይ ራሳቸውን ላዘጋጁ ሰዎች የሚሰጥ ነው» ለሚለው የራሳችን አመለካከት ይሆን ነበር:: ኢየሱስ ግን ከዚህ በፍጹም የተለየ መመሪያን ሰጥቶአል:: ይህም:- «በእናንተ ዘንድ ግን እንዲህ አይደለም» የሚል ነው:: መንፈሳዊ አገልግሎት ወይም መሪነት የእግዚአብሔር ሉዓላዊ

ምርጫ ነው። አዲሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ቍጥር 40 ላይ ያለውን ቃል፦ «ይህ ስፍራ የሚሰጠው ቀድሞውኑ እግዚአብሔር ላዘጋጀላቸው ሰዎች ነው» በሚል መልኩ አስቀምጦታል።

አንድ ሰው የቱንም ያህል ጥልቅ ሥነ መለኮታዊ ግንዛቤ ቢኖረው፣ የቱንም ያህል ሥልጠና ቢያደርግ ለውጤታማ መንፈሳዊ መሪነት ብቁ አያደርገውም። በሉላ ክፍል እንደምንመለከተው ደግሞ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ፦ «እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም» ብሎአቸዋል (ዮሐ. 15፡16)። አንድ ክርስቲያን አገልጋይ «እኔ እዚህ ያለሁት በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ምርጫ እንጂ በሰዎች ምርጫ አይደለም» ብሎ መናገር እስከቻለ ድረስ ደፋርና ልበ ሙሉ ይሆናል።

- *መንፈሳዊ መሪነት መከራና ችግርን ማስከተሉ የማይቀር ነው።*

«እኔ የምጠጣውን ጽዋ ልትጠጡ፣ እኔ የምጠመቀውን ጥምቀት ልትጠመቁ ትችላላችሁን? (ማር. 10፡38)።

በመንግሥቱ አገልጋይ መሆን ስለሚያስከፍለው ዋጋ ኢየሱስ በግልጽና ያለ አንዳች ማመንታት አመልክቶአል። የተሰጠውን ከባድ ሥራ ከግብ ለማድረስ እስከ ሞት ድረስ ራሳቸውን የሰጡ ተከታዮች እንደሚያስፈልጉት ሳይደብቅ ነግሮአቸዋል። ጌታ ላቀረበው ጥያቄ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት በችኮላ የሰጡት መልስ «አዎን፣ እንችላለን» የሚል ነበር። ይሁን እንጂ ስለ ራሳቸው ያላቸው ግንዛቤ ምን ያህል ደካማ መሆኑን አሳይተዋል። ኢየሱስም ጽዋውን መጠጣት ጥምቀቱንም መጠመቅ እንደሚችሉ ነገሮአቸዋል። መንፈሳዊ መሪነት የሚያስከፍለውን ክቡር ዋጋ በተግባር መማር ነበረባቸው። ከታሪክ እንደምንመለከተው ያዕቆብ አንገቱን በመቀላት ተገድሎአል፤ ዮሐንስም እስር ቤት እያለ ነበር የሞተው።

በአቋራጭ ወይም በቀላል መንገድ የመንፈሳዊ መሪነትን ሥልጣን መጨበጥ እንደሚችሉ ቢያስቡም፣ ኢየሱስ የሰጣቸው መልስ ግን ፍጹም ያልጠበቁት ነበር። ትልቅነት የሚገኘው አገልጋይ በመሆን ነው፤ ግንባር ቀደሙን ስፍራ መያዝ የሚቻለው የሁሉም ባሪያ በመሆን ነው፤ ይህ ደግሞ አስደንጋጭ ሆኖባቸዋል።

የደቀ መዛሙርቱን እግር ባጠበ ጊዜ ኢየሱስ መመሪያ ሊያደርጉት የሚገባ ምሳሌ ሰጥቶአቸዋል። ይህም አገልጋይ ወይም ባሪያ መሆን ነበር (ዮሐ. 13፡15)። ሐዋርያ ጴጥሮስ ደግሞ ኢየሱስ የተወልን ምሳሌ መከራ መቀበልን እንደሆነ አመልክቶአል (1ኛ ጴጥ. 2፡21)። ስለሆነም አገልጋይነትና መከራ መቀበል የተያያዙ ነገሮች መሆናቸውን ከጌታ

ኢየሱስ ሕይወት መረዳት ይቻላል ማለት ነው። እንዲህ ከሆነ ታዲያ፣ አገልጋይ ከጌታው ይበልጣል ብላችሁ ታስባላችሁ?

ላቅ ያለ የመሪነት ሥልጣንን ማግኘት የሚቻለው ሌሎችን በማገልገል እንደሆነ ኢየሱስ ሲናገር በጠማማ መንፈስ ተነሣሥተው ሌሎችን የሚያገለግሉ እንኳ ቢሆኑ ይህን ያገኛሉ ማለቱ አልነበረም። ኢየሱስ ይህን ያለው የአገልጋይነት መንፈስን ለማሳየት ነበር፤ ስለ ራሱ ሲናገር «በመካከላችሁ እንደ አገልጋይ ነኝ» አለ።

ስለ መሲሑ አገልግሎትና ማንንት ከሚናገሩ ምዕራፎች አንዱ የሆነው ኢሳይያስ 42:1-5 የአገልጋይነት መንፈስ ምን እንደሆነ ዝርዝር መመሪያዎችን ያቀርባል። የእግዚአብሔር ባሪያ ወይም አገልጋይ እንደመሆኑ መጠን ወደ ፊት የሚመጣው መሲሕ እነዚህን መስፈርቶች አሟልቶ መገኘት ነበረበት።

በእነርሱ በኩል ራሱን ለዓለም ለመግለጥ አገልጋዮቹ እንዲሆኑ እግዚአብሔር እስራኤልን መርጦ ነበር። ይሁን እንጂ፣ ሕዝበ እስራኤል በእርሱ ዓላማና እቅድ መሠረት አልኖሩም። እስራኤል ታማኝ ባይሆኑም ኢየሱስ ግን መስፈርቱን አሟልቶ ተገኝቶአልና አገልግሎትን በተመለከተ ለእያንዳንዳችን ምሳሌ ሊሆነን ይችላል። ኢየሱስ ካሟላቸው መስፈርቶች ጥቂቶቹ፦

በራሱ ሳይሆን በእግዚብሔር ይደገፍ ነበር

«እነሆ፣ እኔ ደግፌ የያዝሁት ባሪያዬ. . .» (ቍ. 1) የሚለው መሲሑ ምን ያህል በእግዚአብሔር ይደገፍ እንደነበር ያመለክታል። በተነገረለት ትንቢት መሠረት ኢየሱስ በፈቃደኝነት «ራሱን ባዶ አደረገ» (ፊልጵ. 2:7)። በራሱ ፈቃድ የመኖር መብቱን ተወ። እንደ አምላክነቱ ኃይልና ሥልጣን ቢኖረውም በፍጹም ልቡ በእግዚአብሔር አባቱ ይደገፍ ነበር «ሁሉን በሥልጣኑ ቃል» ደግፎ ያቆመ ቢሆንም (ዕብ. 1:3) እርሱ ግን ከኃጢአት በቀር ከደካሞቹ የሰው ልጆች ጋር አንድ መሆንን መረጠ፤ ስለሆነም እንደ ደካማ ሰው በእግዚአብሔር መደገፍ ተገባው። እኛም ብንሆን መንፈስ ቅዱስ የሚጠቀምብን በእግዚአብሔር በተደገፍንበት መጠን መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል።

በእግዚአብሔር የተመረጠ ነበር

«ነፍሴ ደስ የተሰኘችበት ምርጤ» (ቍ. 1) እግዚአብሔር በእርሱ ደስ የመሰኘቱን ያህል ከሌላ ክፍል እንደምንመለከተው አገልጋዩ ደግሞ «ፈቃድህን ላደርግ ወደድሁ» አለ (መዝ. 40:8)።

የጭምትነት ሕይወት ኖረ

«አይጮኽም፤ ቃሉንም አያነሣም፤ ድምፁንም በሜዳ አያሰማም» (ቊ. 2)። የእግዚአብሔር ባሪያ አገልግሎት ጭምትነትና ራስን መግዛት ላይ እንጂ ጫጫታና ግርግር ላይ የተመሠረተ አልነበረም። ሰዎች ራሳቸውን ለማስተዋወቅ ብዙ ላይ ታች በሚሉበት በዚህ ዘመን ይህ ባሕርይ እጅግ አስፈላጊ ነው።

ዲያብሎስ ኢየሱስን በፈተነው ጊዜ ከቤተ መቅደስ ጫፍ ላይ ተወርውሮ እንዲወድቅ ጠይቆት ነበር። ኢየሱስ ያንን ቢያደርግና በተአምር ቢተርፍ ኖሮ በሕዝቡ ዘንድ አድናቆትና መገረምን ያገኝ ነበር፤ እርሱ ግን እንደዚያ አላደረገም።

የእግዚአብሔር አገልጋይ መኖሩ እንኳ በማይታወቅበት ሁኔታ በጸጥታና በእርጋታ የተሰጠውን ኃላፊነት ይፈጽማል። ኢሳይያስ 45፡15 «በእውነት አንተ ራስህን የምትሰውር አምላክ ነህ» ይላል። መሲሑም እንዲሁ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈጸመ እንጂ ልታይ ልታይ የሚል ባሕርይን አልጸባረቀም። ከመላእክት ወገን የሆኑት ሱራፌል ስድስት ክንፎች አሉአቸው፤ ከስድስቱ አራቱን የሚጠቀሙባቸው ፊታቸውን ለመሸፈን ነበር፤ ይህም በስውር የሚደረግ አገልግሎትን የሚያመለክት ምሳሌ ነው።

ሩጎሩጎና አዛኝ ነበር

«የተቀጠቀጠ ሸንበቆን አይሰብርም፤ የሚጤስ ጧፍንም አያጠፋም» (ቊ. 3)። የእግዚአብሔር ባሪያ ዓይነተኛ ምልክቱ የሰዎችን ደካማነትና ጉድለት በርኅራኄ መቀበሉ ነበር። ሰዎች ደካማና አቅመ ቢሶችን ረግጠዋቸው ያልፋሉ፤ እውነተኛ አገልጋይ ግን ይህን አያደርግም። የተጠቀጠ ሸንበቆን ይጠግናል፤ እየጤሰ ያለ ጧፍን እንዲያበራ ያደርገዋል። ብዙ ክርስቲያን አገልጋዮች የደከሙና የወደቁትን ገለል በማድረግ ያልፉዋቸዋል። ዋናው ትኩረታቸው የሰዎችን ትኩረት መሳብ የሚያስችላቸው አገልግሎት ላይ በመሆኑ ከደካሞች ጋር ጊዜ ማጥፋት አይፈልጉም፤ እውነተኛ አገልጋይ ግን የወደቁትን ያነሣል፤ የተሰበሩትን ይጠግናል እንጂ በቸልታ አያልፍም።

ባለ ብሩህ ተስፋ እንጂ ጨለምተኛ አልነበረም

«ፍትሕን በምድር እስኪያመጣ ድረስ አይደክምም፤ ተስፋም አይቆርጥም» (ቊ. 4 አ.መ.ት)። የእግዚአብሔር አገልጋይ በምንም ዓይነት ተስፋ አይቈርጥም። በትንሽ በትልቁ ተስፋ የሚቆርጥ መሪ ራሱ ተነቃቅቶ ሌላውን አያነቃቃም። እንደሚታወቀው የጨለማ ኃይላት የሰዎችን ነፍስ ለመቀራመት የሞት የሽረት ትግል እያደረጉ

ነው፡፡ ስለሆነም ባለተስፋ መሆንና የነገሮች ብሩህ ገጽታ መመልከት ከአንድ አገልጋይ እጅግ የሚፈለጉ ባሕርያት ናቸው፡፡ ዓላማው እስኪፈጸምና ግቡ ላይ እስኪደርስ ድረስ የእግዚአብሔር አገልጋይ በፍጹም ተስፋ አይቁርጥም፡፡

በእግዚአብሔር የተቀባ ነበር

«መንፈሴን በእርሱ ላይ አድርጋለሁ»» (ቁ. 1) እስካሁን ድረስ የተመለከትናቸው አምስት ባሕርያት አገልጋዩ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት እንዲወጣ በማድረግ ረገድ በራሳቸው ብቁ ወይም የተሟሉ ናቸው ማለት አይቻልም፡፡ እንዲህ እንዲሆን ከተፈለገ በመለኮታዊ ኃይል መዳሰስ አለበት፤ በመንፈስ ቅዱስ መቀባት አለበት፡፡ «እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በኃይልም ቀባው፤ እርሱም መልካም እያደረገ ለዲያብሎስ የተገዙትን ሁሉ እየፈወሰ ዞረ» (የሐዋ. 10:38)፡፡

ምሳሌ የሚሆነን የእግዚአብሔር አገልጋይ የተቀበለውን ቅባት እኛም መቀበል እንችላለን፡፡ በዮርዳኖስ ሲጠመቅ መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ላይ እስኪወርድ ድረስ በናዝሬት ምንም ዓይነት ግርግር ሲፈጥር አንመለከትም፡፡ ዓለምን ማናወጥ የቻለ አገልግሎቱን የጀመረው መንፈስ ቅዱስ ከወረደበት በኋላ ነበር፡፡ ታዲያ፣ አገልጋይ ከጌታው የሚበልጥ ይመስላችኋል? በዚህ ምድር የነበረውን አገልግሎት ፍሬያማ በሆነ ሁኔታ ለመፈጸም ለኢየሱስ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ካስፈለገው ለእኛ አያስፈልገንም ትላላችሁ?

4

የተፈጥሮ ችሎታና መንፈሳዊ መሪነት

ወደ እናንተ በመጣሁ ጊዜ. . . ቃሌም ስብከቴም መንፈስና ኃይልን በመግለጥ ነበረ እንጂ በሚያባብል በጥበብ ቃል አልነበረም
1ኛ ቆሮንቶስ 2:1፣ 4::

መሪነት ማለት ሰዎች ላይ በጐ ተፅዕኖ ማሳደር ማለት ነው፤ የሌሎችን ዝንባሌ እርሱ ወደሚያምንበት አቅጣጫ መለወጥ ማለት ነው:: አንድ ሰው ሌሎችን መምራት የሚችለው እነርሱን ወደ ራሱ መንገድና አመለካከት ማምጣት እስከቻለ ድረስ ነው:: በነበራቸው የአመራር ችሎታ ሌሎች ላይ በጐ ተጽዕኖ ማሳደር የቻሉ ሰዎች ስለ መሪነት የሰጡት ገለጻም ይህንኑ የሚደግፍ ሆኖ ተገኝቶአል:: ላቅ ባለ ወታደራዊ አመራር ችሎታቸው አውቅናን ያገኙት ሎርድ ሞንትጐመሪ መሪነትን በሚከተለው ሁኔታ ገልጸውታል:- «ለአንድ የጋራ ዓላማ ሰዎችን ማነሣሣት መቻል፣ ሌሎች እምነታቸውን የሚጥሉበት ዓይነት ሰው ሆኖ መገኘት::» የእንግሊዙ ጠቅላይ ሚኒስትር ዊንስተን ቸርችል ለዚህ ዓይነተኛ ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ::

አንድ ሌላ ሰው ደግሞ «የእርሱን አሳብ ተቀብለው የሚሰጣቸውን ትእዛዝ ለመፈጸም ዝግጁ እንዲሆኑ ሰዎች እምነት የሚጥሉበት ሆኖ የመገኘት ብቃት» በማለት መሪነትን ገልጸዋል::

ጄኔራል ቻርለስ ጐርደን የተባሉ ሰው ስለ መሪነት ያላቸውን አመለካከት እንዲነግራቸው ለአንድ ቻይናዊ መሪ ሁለት ተያያዥነት ያላቸው ጥያቄዎችን አቅርበው ነበር:: ጥያቄዎቹ «የአመራር ብቃት ምን ማለት ነው? ሰዎችስ በስንት ይመደባሉ?» የሚሉ ሲሆኑ ቻይናዊው መሪ - «ሰዎችን በሦስት ምድቦች ማስቀመጥ ይቻላል:- እነርሱም በምንም ነገር የማይንቀሳቀሱ፣ የሚንቀሳቀሱና ሌሎችን ማንቀሳቀስ የሚችሉ» የሚል አጭርና ቁርጥ ያለ መልስ ሰጥተዋል::

ወንጌልን በማዳረስ ረገድ በወጣቶች መካከል ከፍተኛ ሥራን ያከናወኑ አንድ ሌላ ሰው ደግሞ ስለ መሪነት ሲናገሩ «መሪ ማለት መንገዱን የሚያውቅ፣ በመንገዱ የሚሄድና ሌሎችም በመንገዱ እንዲሄዱ የመሳብ ችሎታ ያለው ሰው ነው» ነበር ያሉት:: ሌላ፣ ሰው ደግሞ ክርስቲያናዊ መሪነትን «ሌሎችን ለመባረክ ሲባል ሰብዓዊውና መለኮታዊው በአንድነት የሚሠሩት ሥራ» ብለውታል::

ከፖለቲካው አንጻር ፕሬዚዳንት ትሩማን መሪነትን በተመለከተ ሲናገሩ፡- «ሰዎች ባይወዱትም እንኳ እርሱ የፈለገውን እንዲያደርጉ የሚያነሣሣና በጊዜ ሂደትም የሚያደርጉትን እንዲወዱ የማድረግ ችሎታ» ብለዋል።

መንፈሳዊ መሪነት በተፈጥሮ የታደልናቸው ስጦታዎችና ከእግዚአብሔር የተቀበልናቸው ባሕርያት በጥምር ሲሠሩ ማለት ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ በተፈጥሮ የታደልናቸው ስጦታዎች እንኳ ከእግዚአብሔር ተቀበልናቸው እንጂ የእኛ አይደሉም፣ ለእግዚአብሔር አገልግሎትና ክብር ስንጠቀምባቸው ግን ይበልጥ ውጤታማ ይሆናሉ፤ ላቅ ያለ ተግባርንም ያከናውናሉ። ከላይ የተመለከትናቸው ገለጻዎች አጠቃላይ በሆነ መልኩ ስለ መሪነት የሚገልጹ ናቸው። ምንም እንኳ እነዚህ ባሕርያት ለመንፈሳዊ መሪነት የራሳቸው ድርሻ ቢኖራቸውም የሚጠበቅባቸውን ውጤት እንዲያስገኙ ከተፈለገ በእነርሱ ላይ የምንጨምራቸውና ቅድሚያ የምንሰጣቸው ሌሎች ባሕርያትም ይኖራሉ። በተፈጥሮ በምንታደለው የመሪነት ችሎታ ውስጥ ሰብዕና ራሱን የቻለ ስፍራ አለው። «ሰዎችን የማነሣሣትና የመማረክ ችሎታ የሚወሰነው ባለን መልካም ባሕርይ መጠን ነው። እንዲህ ባለው ሰው ውስጥ የሚቀጣጠለው ብርሃን ሌሎችን ይመራል፤ ሰዎችን የመሳብ ችሎታውም በእርሱ እንዲማረኩ ያደርጋል።»

መንፈሳዊ መሪ ግን ሰዎችን መማረክ የሚችለው በራሱ ሰብዕና ብቻ ሳይሆን የግለሰቡ ሰብዕና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሲነቃቃና ሲነሣሣ ጭምር ነው። ሙሉ በሙሉ ሕይወቱን ለመንፈስ ቅዱስ ቍጥጥር አሳልፎ በመስጠቱ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ያለ አንዳች መከልከል በሕይወቱ ይሠራል፤ ለሌሎችም ይተርፋል።

መንፈሳዊ መሪነት የመንፈሳዊ ኃይል ውጤት ስለ ሆነ ጨርሶ ከሰዎች የሚመነጭ አይደለም። ማንም በፈለገው ጊዜ ተነሥቶ ራሱን መንፈሳዊ መሪ ማድረግ አይችልም። ከሚመራቸው ሰዎች በተለየ ሁኔታ መንፈስ ቅዱስ በእርሱ አማካይነትና በእርሱ ውስጥ በመሥራቱ በመንፈሳዊ መልኩ ሰዎችን ይማርካል።

አጠቃላይ በሆነ መልኩ ስንመለከተው ሌሎችን መምራት ወይም መማረክ የምንችለው እኛ ራሳችን እስከ ደረስንበት መንፈሳዊ እድገት ድረስ ነው ማለት ይቻላል። ስለዚህም አንድ ሰው ውጤታማ የሚሆነው «በዚህ ሂዱ» ብሎ መንገዱን በማመልከቱ ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ጋር በዚያ መንገድ አብሮ ሲጓዝ ነው። መሪዎች የምንሆነው ሌሎችን ለማነሣሣትና እንዲከተሉን ማድረግ በቻልንበት መጠን ነው።

የተፈጥሮ ችሎታና መንፈሳዊ መሪነት

አንድ ጊዜ በቻይና ተሰብስበው የነበሩ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲናት መሪዎች የመሪነት ችሎታን በተመለከተ እየተወያዩ ነበር። የጋለ ውይይትና ክርክር እየተካሄደ እያለ የአንድ መንፈሳዊ ድርጅት መሪ ግን በጸጥታ ሁኔታውን እየተከታተሉ ነበር። ይህን ያስተዋለ የጉባኤው ሊቀ መንበር የሚናገሩት ነገር ካላቸው እንዲናገሩ እኚህን ሰው ይጋብዛቸዋል። ይህን የሰሙ የጉባኤው ታዳሚዎችም የእኚህን ሰው ቁም ነገረኛነት ቀደም ብለው ያውቁ ስለ ነበር በቀረበላቸው ግብገር ደስ ብሎአቸው የሚናገሩትን ለመስማት ይቁነጠነጡ ነበር። እርሳቸውም ወደ መድረኩ ወጡና ረጋ ባለ ሁኔታ፡- «እኔ እንደማስበው ከሆነ አንድ ሰው መሪ የመሆን ብቃት አለው የምለው ተከታዮች ሲኖሩት ነው» አሉ።

መሪዎች መሪ ሆነው ይወለዳሉ ወይስ በኋላ የሚያገኙት ችሎታ ነው?

የመሪነት ችሎታ ከሰዎች ጋር አብሮ የሚወለድ ነው ወይስ ከተወለዱ በኋላ የሚያገኙት ችሎታ ነው? ለሚለው ጥያቄ የተለያዩ መልሶች ተሰጥተዋል። ትክክለኛው መልስ ግን «ሁለቱም የየራሳቸው ድርሻ አላቸው» የሚል ነው። በአንድ በኩል የመሪነት ችሎታ በቀጥታ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ መሆኑ ሲነገር ኖሮአል። በሌላ በኩል ደግሞ እንደማንኛውም ችሎታ ሁሉ መዳበር ያለበት መሆኑ ግልጽ ነው። ማንኛችንም ብንሆን ከተወለድንበት ጊዜ አንሥቶ ለአንዳንድ ሥራዎች ብቁ የሚያደርጉን ባሕርያት ይኖሩናል። አንድ አስቸጋሪ ሁኔታ ተከስቶ እነዚህ ባሕርያት ይፋ እስኪሆኑ ድረስ ግን በውስጣችን ተዳፍነው ይኖራሉ።

የአንዳንድ ሰዎች የመሪነት ችሎታ የሚታየው የተለያዩ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲገጥሙዋቸውና መፍትሔ የሚሰጥ ሰው በአጠገባቸው በማይኖርበት ጊዜ ይመስላል። ይሁን እንጂ፣ የእነዚህን ሰዎች ሕይወት ስናጠና ማንም ሳያውቀው በተለያየ ሥልጠና ውስጥ ያልፉ እንደነበር ግልጽ ይሆንልናል፤ የረጅም ጊዜ ሥልጠናና ውጣ ውረድ ውጤት እንጂ እንደዚሁ በአጋጣሚ የተገኘ አይደለም። ዮሴፍ ለዚህ ዓይነተኛ ምሳሌ ሊሆን ይችላል። የግብጽ ጠቅላይ ሚኒስትር ለመሆን የበቃው በአጋጣሚ ወይም በድንገት አልነበረም፤ ማንም ሳያይና ሳያውቅ እግዚአብሔር ዮሴፍን አሥራ ሦስት ዓመት ሙሉ ሲያዘጋጀው ነበር። ተፈጥሮአዊና መንፈሳዊ የመሪነት ችሎታ ብዙ የሚመሳሰሉባቸው ነጥቦች ቢኖሩም አንዳንድ በጣም የሚለያዩባቸው ነጥቦች እንዳሉም ግልጽ ነው። ይህንንም ከሚከተለው ንጽጽር መመልከት ይቻላል።

ተፈጥሮአዊ	መንፈሳዊ
- በራሱ ይተማመናል	- በእግዚአብሔር ይተማመናል
- ሰዎችን ያውቃል	- እግዚአብሔርንም ያውቃል
- በራሱ ተነሣሥቶ ውሳኔ ያደርጋል	- በሁኔታዎች ሁሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መረዳት ይፈልጋል።
- ለራሱ ታላቅ ነገርን ይመኛል	- ራሱን የካደ ነው
- በራሱ ዘዴና ጥበብ ይደገፋል	- በእግዚአብሔር ዓላማና መንገድ ይደገፋል
- ሌሎችን ማዘዝ ደስ ይለዋል	- ለእግዚአብሔር መታዘዝን ይፈልጋል
- ለራሱ ጥቅም ለሚያስገኝለት ነገር ይሯሯጣል	- እርምጃው ሁሉ እግዚአብሔርንና ሰዎችን ከመውደዱ የተነሣ ነው
- የራሱን መንገድ መከተል ይፈልጋል	- የእግዚአብሔርን መንገድ መከተል ይፈልጋል።

ምንም እንኳ በጌታ በማመኑ ብቻ አንድን ሰው መሪ ይሆናል ማለት ባይቻልም ሙሉ በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ ሲደገፍ ግን በአስፈላጊው ሰዓት መንፈስ ቅዱስ የመሪነትን ጥበብ ሊሰጠው እንደሚችል ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ መመልከት ይቻላል። መንፈሳዊ ስጦታዎችን ማደል የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው፤ እነዚህን ስጦታ የተቀበለ ሰው ደግሞ ውጤታማ የመሪነት ችሎታ ይኖረዋል።

ኤ. ደብልዩ ቶዘር የተባሉ የእግዚአብሔር ሰው ይህን በተመለከተ፡-

> እውነተኛ መሪ ሌሎችን የመምራት ፍላጐት የለውም፤ ውስጣዊ የመንፈስ ቅዱስ ምሪትና ውጫዊ ጫናዎች ግን ያን ሰው መሪ እንዲሆን ያስገድዱታል። ከሙሴና ከዳዊት እንዲሁም ከብሉይ ኪዳን ነቢያት የምንመለከተው ይህንኑ ነው። ከጳውሎስ ጀምረን እስከ ዘመናችን ያሉትን ታላላቅ መሪዎች ሕይወት ብንመረምር ለዚያ ኃላፊነት ያነሣሣቸው መንፈስ ቅዱስ እንጂ እነርሱ ፍላጐት ወይም ዝንባሌ እንዳልነበራቸው እንረዳለን። ስለሆነም መሪ መሆንን አጥብቆ የሚመኝ ሰው መሪ መሆን የለበትም ብንል እውነትነት አለው ማለት ነው። እውነተኛ መሪ

የእግዚአብሔር በሆነ ነገር ላይ ሌሎችን ከመጫን ይልቅ ትሑት፣ ጨዋና ራሱን የካደ ነው፤ ከእርሱ የተሻለ ችሎታና አስተዋይነት ያላቸው ሰዎች መኖራቸውን መንፈስ ቅዱስ ግልጽ ሊያደርግለትም አሳባቸውን ለመቀበል ዝግጁ ይሆናል።

ዊልያም ኢ.ሳንግስተር ከተባሉ የሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴ መሪ የሕይወት ታሪክ እንደምንመለከተው እርሳቸው ከሞቱ በኋላ በተገኘ የግል ማስታወሻቸው የሰፈረ አሳብ ይህንኑ የሚደግፍ ነው። እኚህ ሰው በእንግሊዝ አገር የነበረችው ቤተ ክርስቲያን መሪ እንዲሆኑ በየጊዜው እያደገ ስለመጣው ፍላጐታቸው ሲናገሩ እንዲህ ብለው ነበር፦

ይህ እግዚአብሔር ለሕይወቴ ያለው ዓላማና እቅድ እንደሆነ አምናለሁ። በፍጹም አልመረጥሁትም፤ እንዲያውም ልሸሸው ፈልጌ ነበር፤ ግን አልሆነልኝም። በወንጌል ሰባኪነት ሥራ ብቻ እንድወሰን የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳልሆነ በጥልቅ እኔነቴ ውስጥ ይሰማኛል፤ የሕዝቡ መሪ እንድሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ ለመሆኑ ከምንጊዜውም በላይ እርግጠኛ ሆኜአለሁ። ስለሆነም የራሴን ክብርና ፍላጐት ግምት ውስጥ ሳላስገባ፣ በዕድሜ የሚበልጡኝና በቅንዓት የተነሣሡ ሰዎች ለሚሰነዝሩት ትችት ሳልንበረከክ በማንኛውም መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ከእርሱ በታች መሪ በመሆን ላገለግለው ወስኛለሁ።

በአሁኑ ጊዜ ሰላሣ ስድስት ዓመቴ ነው። በዚህ መንገድ እንዳገለግለው የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ በፍጹም ልቤ ከመታዘዝ ውጪ ሌላ አማራጭ አይኖረኝም።

ምናልባት የራሴ ምኞትና ከንቱ ፍላጐት ይኖርበት ይሆን? በማለት ልቤን በሚገባ መርምሬአለሁ፤ ሆኖም እንዲህ ያለ ዝንባሌ አላገኘሁም። ከሰዎች ነቀፋና ትችት እንደሚሰነዘርብኝ አውቃለሁ፤ ይህም በጣም የምጠላው ነው። በሰዎች ታዋቂ የመሆን ፍላጎት የለኝም፤ ይልቁንም ፍላጐቴ በጣም ጥቂት ከሆኑ ሰዎችና ከምወዳቸው መጻሕፍት ጋር ማሳለፍ ነበር፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ ግን እንዲህ ሆኖአል። እግዚአብሔር ይረዳኝ።

በዚህ ጥሪ ግራ ተጋብቼ እያለሁ <ቃሌን በአንተ በኩል ማስተላለፍ እፈልጋለሁ> የሚል የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰማሁ። ጌታ ሆይ፣ አንተ ከሰጠኸው ሥራ ሸሽቶ ያመለጠ

የትኛው ሐዋርያ ነው? 'እምቢ' ማለት እንደሌለብኝ ይገባኛል፤ ሆኖም እንደ ዮናስ ለመሸሽ ቃጥቶኝ ነበር።

መንፈሳዊ መሪነትና ሥልጣንን በምንም ዓይነት በተፈጥሮ ችሎታና ዝንባሌ መለካት እንደማይቻል ከቅዱስ ፍራንሲስኮ ሕይወት መመልከት ይቻላል። አንድ ጊዜ አንድ ሰው «እንደምናውቀው መልክ ቀና አይደለህም፤ የተማርህና የትልቅ ሰው ዘርም አይደለህም። ሆኖም ሰው ሁሉ ይከተልሃል፤ ሰው ሊያይህና ሊከተልህ ይፈልጋል። ዓለም ሁሉ እንዲከተልህ ያደረገው ምንድን ነው? በማለት በፌዝና በንቀት መልክ ደጋግሞ ይጠይቀዋል።

ቅዱስ ፍራንሲስኮም ይህን ሲሰማ በጣም ደስ አለው፤ ዓይኖቹን ወደ ሰማይ አቀና፣ ለረጅም ጊዜ በተመስጦ ከቆየ በኋላ ተንበርክኮ እግዚአብሔርን አመሰገነ። ጥያቄውን ወደቀረበለት ወንድም ዘወር ብሎ፦

> «ምክንያቱን ማወቅ ትፈልጋለህ? ምክንያቱማ እንዲህ እንዲሆን በልዑል አምላክ ተወስኖአል። ዓይኖቹ መልካሙንና ክፉውን ይመረምራሉ፤ ከኃጢአተኞች መካከል ከእኔ የባሰ ኃጢአተኛ፣ ከትንንሾች መካከልም ከእኔ የባሰ ታናሽ ማግኘት አልቻለም፤ ስለሆነም ይህን ታላቅ ሥራ እንድፈጽም መረጠኝ። የመረጠኝ ከእኔ የባሰ ዋጋ ቢስ ሰው በማጣቱ ነው። ታላላቆችና ስመ ጥር የሆኑትን ለማሳፈር መረጠኝ፤ የዓለምን ጉልበት፣ ውበትና እውቀት ባዶ ለማድረግም እኔን መረጠኝ»። በማለት መልሶለታል።

በነበራቸው ጥበብና ማስተዋል የመሪነት ችሎታቸውን ካስመሰከሩ ሰዎች ብዙ የምንማረው ይኖረናል። ቀደም ሲል የተጠቀሱት ሁለት ሰዎች ትክክለኛ መሪን በተመለከተ የየራሳቸው መለኪያ መስፈርት ነበራቸው።

አንደኛው ሎርድ ሞንትጉመሪ የተባሉ የጦር መሪ ሲሆኑ፣ በጦርነት ወቅት ሠራዊትን በመምራት ላይ ያለ ሰው ሊያሟላቸው ስለሚገባ ሰባት ነጥቦች ዘርዝረዋል፤ መንፈሳዊ ውጊያን በተመለከተ እነዚህ ነጥቦች ዐቢይ ድርሻ ስላላቸው አንድ በአንድ እንመለከታቸዋለን። (1ኛ) ከኋላ ሆኖ ሁኔታዎችን ይከታተላል እንጂ ዝርዝር ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ አይገባም። (2ኛ) አስተሳሰቡ ጠባብ ስላልሆነ ለጥቃቅን ነቀፋዎችና ትችቶች ደንታ የለውም። (3ኛ) ልታይ ልታይ ባይና ጉረኛ አይደለም። (4ኛ) ለእያንዳንዱ ሥራና ኃላፊነት የሚመጥኑ ሰዎችን መምረጥ ያውቃል። (5ኛ) አብረውት በሚሠሩ

ለዎች ላይ እምነት ስላለው ያበረታታቸዋል እንጂ ሁሉንም እኔ ካላደረግሁት አይልም። (6ኛ) ግልጽና ጥርት ያለ ውሳኔ የማሳለፍ ብቃት አለው። (7ኛ) ሰዎች እምነታቸውን እንዲጥሉበት ማድረግ ይችላል።

ቀጥሎ ያሉት ደግሞ ከተማሪዎች ጋር ወይም በተማሪዎች መካከል ይሠሩ የነበሩ ሰው ናቸው፤ የተማሪዎችን ችሎታና ማንነት ለመመዘን የሚከተሉትን ዘጠኝ፣ ጥያቄዎችን ያቀርቡ ነበር። (1ኛ) ትናንሽና ጥቃቅን የሚመስሉ ነገሮችን በጥንቃቄ ይሠራልን? (2ኛ) ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ነገሮች ቅድሚያ መስጠትን ያውቃልን? (3ኛ) ትርፍ ጊዜውን በምን መልኩ ነው የሚጠቀምበት? (4ኛ) የጀመረውን ሥራ ለማጠናቀቅ በትጋት ይሠራል ወይስ ጀምሮ ያቋርጣል? (5ኛ) ያልተጠበቁ ሁኔታዎችና አጋጣሚዎችን በሚገባ ማስተናገድ ይችላል? (6ኛ) የማደግና በየጊዜው ልቆ የመገኘት ዝንባሌ ይታይበታል? 7ኛ. ተስፋ አስቆራጭ ለሆኑ ነገሮች ምን ዓይነት ዝንባሌ አለው? (8ኛ) የማይቻሉ የሚመስሉ ነገሮች ሲገጥሙትስ እንዴት ይቋቋማቸዋል? (9ኛ) ደካማ ጐኖቹ ምንድን ናቸው?

በመሠረተ አሳብ ደረጃ መሪነት ማለት አንድ ሰው በሌላው ላይ ማሳደር የሚችለው ተጽዕኖ ማለት ቢሆንም ይህን ችሎታውን ለመልካም ሆነ ክፉ ሊጠቀምበት እንደሚችል መዘንጋት የለብንም። ማንም ከዚህ ነጻ ሊሆን እንደማይችል ቅዱሳት መጻሕፍትም ሆኑ የሕይወት ተሞክሮ የሚያረጋግጡት ሐቅ ነው። ብናውቀውም ባናውቀውም አብረውን ባሉ ሰዎች ላይ የምናሳድረው ተጽዕኖ ይኖራል። እነርሱም እንዲሁ እኛ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ። ለምሳሌ ያህል ዶክተር ጌዲ የተባሉ ሰው በ1848 ዓ.ም ከአገራቸው ውጪ ለሃያ አራት ዓመት እግዚአብሔርን ሲያገለግሉ ኖረው ነበር። ለመታሰቢያቸው እንዲሆን በተዘጋጀ አንድ ሰሌዳ ላይ የሚከተለው ቃል ሰፍሮአል፦

- በ1848 ዓ.ም ወደዚያ አገር ሲሄዱ አንድ ክርስቲያን እንኳ አልነበረም።
- በ1872 ዓ.ም ከዚያ ሲወጡ ግን አንድ ክርስቲያን ያልሆነ ሰው ማግኘት አልተቻለም።

ሐዋርያት ይመሩዋት በነበረችው ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እጅግ ብዛት ያላቸው ሰዎች በጌታ አምነዋል፤ መንፈሳዊ መሪነት ማለት ምን ማለት እንደሆነም መንፈስ ቅዱስ በጣም ጠቃሚ ትምህርት ሰጥቶአል። የሥራቸው ኃላፊነትና ጫና በጣም ከባድ ከመሆኑ የተነሣ ከእነርሱ

በታች ሆነው የድሆችና የመበለቶችን ጉዳይ የሚከታተሉ ሰዎችን መምረጥ አስፈልጉአቸው ነበር። እነዚህን ሰዎች ለመምረጥ ሐዋርያቱ እንደ መስፈርት ከተጠቀሙት መመሪያ አንዱ «በመልካም የተመሰከረላቸውን፣ መንፈስ ቅዱስና ጥበብ የሚላባቸውን ሰባት ሰዎች ከእናንተ ምረጡ፤ ለዚህም ጉዳይ እንሾማቸዋለን» የሚል ነበር (የሐዋ. 6:3)።

ምንም እንኳ ሥራው ከፍተኛ መስሎ ባይታይም «መንፈስ ቅዱስ የሞባቸው» ሰዎች ማስፈለጋቸው ያለ ምክንያት ይመስላችኋልን? እምነት የሚጣልባቸውና በመልካም ባሕርያቸው የተመሰከረላቸው መሆን ነበረባቸው፤ መንፈስ ቅዱስና ጥበብ የሞላባቸው ሰዎች መሆን ነበረባቸው። መንፈሳዊ ሕይወትን በቃላት መግለጹ አዳጋች ቢሆንም፣ መንፈሳዊነት ያላቸውና የሌላቸውን ሰዎች ግን በቀላሉ መለየት ይቻላል። አንዳንድ ሰዎች መንፈሳዊ ሕይወትን ከጌታ አትክልት ስፍራ የሚወጣ መልካም መዓዛ በማለት ገልጸውታል። መንፈሳዊ ሕይወት ማለት አካባቢን ወይም ያለበትን ስፍራ የመለወጥ ችሎታ ማለት ነው። እኛ ባናውቀውም እንኳ ክርስቶስንና መንፈሳዊ ነገሮችን ለሌሎች እውን እንዲሆኑ የማድረግ ብቃት ነው።

እንግዲህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዝቅተኛ መስሎ ለሚታይ ሥራ መመዘኛው ይህ ከሆነ ከፍተኛ የኃላፊነት ደረጃ ላይ ካሉት የሚጠበቀውስ ምን ይህል የላቀ ይሆን? መንፈሳዊ ግብ ላይ መድረስ የሚቻለው መንፈሳዊ አሠራርን በሚከተሉ መንፈሳዊ ሰዎች አማካይነት ነው። ይህን መመሪያ ተግባር ላይ አውለነው ቢሆን ኖሮ በቤተ ክርስቲያን ወይም በክርስቲያን ድርጅቶች ምን ያህል አስደናቂ ለውጥ በኖረ ነበር! የቱንም ያህል ችሎታ ያላቸው ቢሆኑም ፣ የቱንም ያህል የሰዎችን ስሜት የመማረክ ዘዴ የተካኑ ቢሆኑም፣ መንፈሳዊነት የሌላቸው ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የኃላፊነት ስፍራ ሊሰጣቸው አይገባም፤ ሌላው ቀርቶ ተራና ጊዜያዊ በሆኑ ነገሮች ላይ ባለሥልጣን መሆን የለባቸውም።

የእውነተኛ መንፈሳዊ መሪ ባሕርያትን በተመለከተ አንድ ሰው እንዲህ በማለት ተናግረዋል -

ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን. . . በማለት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር፡- ያለምንም ስስትና ንፍገት ሌሎችን ማገልገልን፣ በዚህ ዓለም ታላቅን ነገር ለእግዚአብሔር መፈጸምን፣ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት ይመሠረት ዘንድ ያለ ምንም ራስ ወዳድነት መሥራትን፣ በአእምሮው ይዞ ሳይሆን እንዳልቀረ እገምታለሁ።

5

እምቅ የመሪነት ችሎታን እንዴት ማወቅ እንደሚቻል

... በመካከላቸው አለቃ የሆነ አንድ ሰው ትልካላችሁ

ዘኁልቁ 13:2

የወደፊት መሪዎችን ለመምረጥ ጌታ የተጠቀመበት መንገድ በዚያ ዘመንም ሆነ ዛሬ ከሰዎች አስተሳሰብና አመለካከት ጋር ፍጹም የማይግባባ ነው። ምንም ትምህርት የሌላቸውን፣ በማንበረሰቡ ዘንድ ተደማጭነት የሌላቸውን ሐዋርያቱን የመሳሰሉ ሰዎችን ዓለም አቀፍ አንድምታ ላለው ሥራ ማን ሊመርጣቸው ይችላል?

እኛ ብንሆን ኖሮ ለመሪነት የምንመርጠው ታዋቂ ዲፕሎማቶችን፣ ጥልቅ የኤኮኖሚ ግንዛቤ ያላቸውን፣ ስመ ጥር ከሆነ ካህናት የተወለዱትን፣ ከፍተኛ ምሑራንን ወይም የዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰሮችን ይሆን አልነበር? ኢየሱስ ግን ከእንዲህ ዓይነቶቹ አንዱንም አልመረጠም። ደቀ መዛሙርቱ በሙሉ ዝቅተኛ ስፍራ የሚሰጣቸው ነበሩ፤ ከዘመኑ ሥልጣኔና ውስብስብ አኗኗር ርቀው ያሉ እንጂ አንዳቸውም እንኳ ተሰሚነት ያላቸው ወይም ተናግረው ማሳመን የሚችሉ ዓይነቶች አልነበሩም።

ከሃይማኖት፣ ባለሥልጣናት መካከል ሳይሆን ተራ ሰዎችን ነበር የመረጠው። ወደ ቻይና ሄደው በሚስዮናዊነት እንዲያገለግሉ ሐድሰን ቴለር የመረጠው ተራ ሰዎችን ስለነበር በሃይማኖት ሰዎች ዘንድ ከፍተኛ ቅሬታ ፈጥሮ እንደነበር ይታወሳል። ይሁን እንጂ ውጤቱን ዛሬ ላይ ሆነን ስንገመግመው እነዚያ የተናቁ ሰዎች ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገባቸው ግልጽ ነው፤ ያም ሆኖ ግን ዛሬም ቢሆን ያንን መንገድ መከተል አንፈልግም።

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን የመረጠው ከከፍተኛ ምሑራን መካከል አልነበረም፤ ሌላው ቀርቶ ከገበሬዎች መካከል እንኳ አልነበረም፤ ይህም ከሚሰጣቸው ዓለም አቀፋዊ ተልዕኮ እንዳያዘናጋቸው ወይም ወደ ኋላ እንዳይጐትታቸው ታስቦ ሊሆን ይችላል። ደቀ መዛሙርት ሁሉ ከገሊላ እንጂ ከይሁዳ ከተሞች የተገኙ አልነበሩም። ገሊላ የተለያየ አገር ሰዎች የሚኖሩባት ስለ ነበረች እንደ ይሁዳ ወይም እንደ ኢየሩሳሌም

የተከለለች አልነበረችም፤ የገሊላ ሰዎች አዳዲስ አስተሳሰቦችን ለመስማትም ሆነ ለመቀበል ዝግጁ ነበሩ።

ሌላው ቀርቶ ደቀ መዛሙርቱ መደበኛ ትምህርት እንኳ ያላቸው አልነበሩም፤ ይሁን እንጂ በአጭር ጊዜ ውስጥ ታላላቅ ተግባሮችን በማከናወን «አንቱ» የሚሰኙ ሆነዋል።

ምንም እንኳ በገሊላ የተለያዩ አገር ሰዎች ቢኖሩም ከእርሱ በሚያገኙት መመሪያ መሠረት እነማን ጥሩ መሪ ሊወጣቸው እንደሚችል ኢየሱስ በውስጣቸው የነበረውን እምቅ ችሎታ ማየት ችሎ ነበር። በዚያ እምቅ ችሎታ ላይ ደግሞ መንፈሳዊ ቅንዓትና ታማኝነት ታክሎበት ታላላቅ መሪዎች ሊወጣቸው ችሎአል። ይህም ሆኖ ግን ምንም ስሕተት አልፈጸሙም ማለት አይደለም።

ከተፈጥሮ የሚገኙ መልካም ባሕርያት ለመንፈሳዊ መሪነት አያስፈልጉም ማለት ባይቻልም በውስጣችንም ሆነ በሌሎች ውስጥ ያለውን እምቅ የመሪነት ችሎታ መርምረን ማወቁ ብዙ ሊጠቅመን እንደሚችል ግልጽ ነው። ብዙ ሰዎች በውስጣቸው እምቅ ችሎታ እንዳላቸው ቢታወቅም ራሳቸውን በሚገባ ስለ ማይመረምሩ ወይም ስለማያውቁ ስጦታቸው ተዳፍኖ ይቀራል። የሚከተሉት መመሪያዎችን እንደሚገባ ማጥናት በውስጣችን ያለውን እምቅ ችሎታ ለማወቅ ወይም ለመሪነት ብቁ የሚያደርጉን ባሕርያትን ለመረዳት ብዙ ሊጠቅሙን ይችላሉ።

- ራስህን ከአጉል ልማድ አላቅቀሃል? ሌሎችን ለመምራት በመጀመሪያ ራስህን መግዛትና መቆጣጠር ይገባል።
- ነገሮች ባልጠበቅሃቸው አቅጣጫ ሲሄዱ ወይም የሚያናድድ ነገር ሲገጥምህ ራስህን መቆጣጠር ትችላለህ? በእንዲህ ዓይነት ፈታኝ ሁኔታዎች ራሱን መግዛት ወይም መቆጣጠር የማይችል ሰው የሌሎችን ክበሬታ አያገኝም፤ በገ ተጽዕኖ ሊያሳድርባቸውም አይችልም። ስለዚህ አስቸጋሪና ተስፋ አስቆራጭ ነገሮች ቢገጥሙት እንኳ በእርጋታ መቋቋም የሚችል ሰው ሊሆን ይገባል።
- ያለ ማንም ድጋፍ ወይም እገዛ በራስህ የማሰብ ብቃት አለህ? የሌሎችን አሳብ መቀበል ተገቢ ቢሆንም፤ አንድ መሪ ሌሎች በእርሱ ቦታ ሆነው እንዲያስቡለት ወይም በእርሱ ቦታ ሆነው እንዲወስኑለት አይጠብቅም።

- ነቀፋና ትችትን በበጎ ጐናቸው ትቀበላለህ? ነቀፋና ትችት ሊበረታብህ በዓላማህ ጸንተህ ትቆማለህ? ትሑት ሰው የሚሰነዘሩበትን ጥቃቅን ነቀፋና ትችቶች እንኳ ይቀበላል።
- ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታዎችን አዳዲስ አሳቦችን ለማፍለቅ ትጠቀምባቸዋለህ?
- ለሎች እንዲያከብሩህና እምነታቸውን እንዲጥሉብህ ሙሉ ድጋፋቸውንም እንዲሰጡህ ማድረግ ትችላለህ?
- በሥልጣንህ ወይም ባለህ ደረጃ ጫና ሳታደርግ ሰዎች ሥርዓት ያለው ሕይወት እንዲኖሩ የማድረግ ብቃት አለህ? እውነተኛ መሪነት በልብ ውስጥ ያለ መንፈሳዊ ባሕርይ በመሆኑ ሰዎች እንዲሸቆጠቁጡ ለማድረግ የምናሳድረው ጫና አይደለም።
- ለላም አድራጊና ሰላምን ፈጣሪ ነህን? አንዳንድ ጊዜ ጸብና ሁከት ባለበት ቦታ ሰላምን ከማድረግ ይልቅ የራሳችንን ሰላም ይዘን መቆየት ቀላል ነው። እውነተኛ መሪ ግን ተቃራኒ እይታና አስተሳሰብ ቢሰነዘር እንኳ በሁለቱ መካከል መቀራረብ እንዲኖር እርቅ ፈጣሪ ነው፤ በሚያቀርበው እርቅ ፈጣሪ አሳብ ተራርቀው የነበረ ወገኖችን ያቀራርባል።
- አስቸጋሪና ጥንቃቄ በሚሻቸው ነገሮች ላይ ኀላፊነት ቢሰጥህ ያንን ለመወጣት ብቃት አለህ?
- ለዎች እሺ ወይም እምቢ የማለት መብት አላቸው፤ ያም ሆኖ አንዳንድ ከባድ ነገሮችን እንዲያደርጉ ስታዛቸው ደስ ብሎአቸው ይታዘዙሃል?
- አመለካከትህን ወይም የምታቀርበውን አሳብ ቢቃወሙብህ ምን ይሰማሃል? የራስህን ጥቅም ግምት ውስጥ ሳታስገባ የሚተላለፈውን ውሳኔ ደስ ብሎህ ትቀበላለህ? ውሳኔዎችን የምትቀበለው ወይም የማትቀበለው ከሚያስገኙት የጋር ጥቅም አንጻር ነው ወይስ ከግል ጥቅምህ አኳያ? መሪዎች ተቃውሞ ሊገጥማቸው እንደሚችል መጠበቅ አለባቸው፤ በሚደርስባቸው ተቃውሞም አኩራፊ መሆን የለባቸውም።
- በቀላሉ ኀደኝነትን ትፈጥራለህ? በጀመርኸው ኀደኝነትስ ትዘልቃለህ? የሚኖሩህ ታማኝና የልብ ኀደኞች ለመሪነት ብቃትህ ዓይነተኛ ምስክር ሊሆኑ ይችላሉ።
- እውነትም ይሁን ሐሰት ሰዎች በሚሰጡህ ድጋፍና ምስጋና ትኩራራለህ? የለመድኸው ድጋፍና ምስጋና ሲቀርብህስ ለአጭር ጊዜ ቢሆን እንኳ በራስህ የመተማመን ችሎታህ ይቀንሳል?

- በበላይ አለቆችህ ወይም በማታውቃቸው ሰዎች ፊት ስትሆን መሸቆጥቆጥና መርበትበት ይታይብሃል?
- ከበታችህ ያሉ ሰዎች ከአንተ ጋር ሲሆኑ ሙሉ ነፃነት ይሰማቸዋል? እውነተኛ መሪ ሌሎችን ይረዳል፤ በድካማቸውም ይራራል፤ ስለሆነም ሰዎች ከእርሱ ጋር ሲሆኑ ነፃነት ይሰማቸዋል።
- ዘርን፣ መልክንና ደረጃን ግምት ውስጥ ሳታስገባ ሰዎችን ሁሉ ለመቅረብ ደስተኛ ነህ? ወይስ በሰዎች መካከል አድልዎ ታደርጋለህ? ምናልባት አንተ ራስህ ሳታውቀው ዘረኝነት ወይም ወገንተኝነት ይኖርብህ ይሆን? እንዲህ ያለ ሰው በፍጹም መሪ ሊሆን አይገባም።
- ብልህና ጠንቃቃ ነህ? ከመናገርህ በፊት ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ረጋ ብለህ ታስባለህ?
- በዓላማህና በአቋምህ ቆራጥ ነህ? ወላዋይ ሰው መሪ ቢሆን እንኳ ረጅም ጊዜ አይዘልቅም።
- ቅርታና ምሬትን እያስተናገድህ ነው ወይስ ቢያሳዝኑህ እንኳ ሰዎችን ይቅር ለማለት ዝግጁ ነህ?
- ምክንያታዊ በሆነ መልኩ የወደፊቱን ብሩህ በሆነ ሁኔታ ታያለህ ወይስ ስለ ወደፊቱ ያለህ ተስፋ ጨለምተኛ ነው? የወደፊቱን አጨልሞ የሚመለከት ሰው መሪ ሊሆን አይችልም።
- እንደ ጳውሎስ ሁሉ «ይህን አንድ ነገር አደርጋለሁ» በማለት ራእይህን አጥብቀህ ትይዛለህ? ወይስ ይህንንም ያንንም ለመያዝ ትፍጨረጨራለህ? ያሰበው ላይ የሚደርስ ኃይሉንና ትኩረቱን ሁሉ እዚያ ግብ ላይ የሚያውል ሰው ብቻ ነው።

አር.ኢ. ቶምሰን የተባሉ ሰው ደግሞ መሪ የመሆን ብቃት እንዳለን ወይም እንደሌለን ለማወቅ የሚከተሉት ነጥቦች እንደመስፈርት ሊያገለግሉን እንደሚችሉ ይጠቁማሉ፦

- የሰዎች ውድቀትና እምነት ማጉደል ያናውጠናል ወይስ ለበለጠ ነገር ታጥቀን እንድንነሣ ያደርገናል?
- በተገቢው ሁኔታ በሰዎች መጠቀምን እንችላለን ወይም ደግሞ ለተገቢው ጊዜ ተገቢ ሰዎችን እናዘጋጃለን?
- ሰዎች የእኛን መመሪያ እንዲጠብቁ እናደርጋለን ወይስ በራሳቸው የመንቀሳቀስ ብቃት እንዲኖራቸው እንረዳቸዋለን?
- ነቃፊዎችና ተቺዎች ነን ወይስ የምናበረታታና የምናደፋፍር?

እምቅ የመሪነት ችሎታን እንዴት ማወቅ እንደሚቻል

- ችግር ያለበትን ሰው መርዳት እንሞክራለን ወይስ በተቻለ መጠን ከአጠገባችን እንዲርቅ እናደርጋለን?

እነዚህን መመዘኛዎች አቅልለን መመልከት ወይም የሚያመለክቱንን ደካማ ጐን በቸልታ ማለፍ የትም ሊያደርሰን አይችልም። አንድ ነገር ማድረግ አለብን፤ ለተግባር መነሣሣት አለብን። አንዳንድ ደካማ ጐኖችህን ተመልክተህ ከሆነ በመንፈስ ቅዱስ እርዳታና አጋዥነት ለማስተካከል ለምን አሁኑኑ እርምጃ አትወስድም? ለምን አንዳንድ ውድቀቶችህን ለማስተካከል፣ የደከሙና የሰለሉ ነገሮችህን ለማጠናከር ዝግጅት አታደርግም?

ከላይ የተመለከትናቸው ባሕርያት ሁሉ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ይታዩ ነበር፤ እነዚህ ባሕርያት የእያንዳንዱ ክርስቲያን የሰብዕና አካል ይሆኑ ዘንድ የዘወትር ጸሎቱ ሊሆን ይገባል።

የመሪነት ባሕርይ እንዳይኖረን እንቅፋት የሚሆኑ ሌሎች ነገሮች ደግሞ ስሕተትን ከመቀበል ይልቅ ለምን ተነካሁ ባይነትና ራስን ለመከላከል የምናደርገው መከራ ናቸው። ሰዎች ስሕተታችንን ሲነግሩን እውነትነት ሊኖረው ይችላል፤ ራሳችንን ጻድቅ ለማድረግ የምናሳየው መከራ ግን ተጠቃሚዎች እንዳንሆን ያግደናል።

ለራሳችን ውድቀትና በደል ኃላፊነትን ለመውሰድ ፈቃደኛ አለመሆን ወይም ደግሞ በራሳችን ጥፋት ሌሎችን ምክንያት ማድረግ ሰዎች በእኛ ላይ ያላቸውን እምነትና ከበሬታ ያጎድፋል።

ምንም እንኳ አንድ ሰው የመሪነት ችሎታ ቢኖረውም፣ አዳዲስና ገንቢ አሳቦችንም በማፍለቅ የታወቀ ቢሆንም፣ ግትር እስከሆነና ሌሎችን በትዕግሥት መቀበል እስካልቻለ ድረስ ለሥራው ትልቅ እንቅፋት ይሆንበታል፤ በመጨረሻም ሰዎች ሁሉ ይርቁትና ብቻውን ይቀራል።

በነገር ሁሉ ልቆ መገኘት መልካም ቢሆንም ከመጠን በላይ መንጠራራቱ ግን ራሱን የቻለ ችግር ሊያስከትል ይችላል። እንዲህ ያለ ሰው ከአቅሙ በላይ የሆኑ ግቦችን ያልማል፤ ያሰበው ግብ ላይ መድረስ ሳይሆንለት ከቀረ ደግሞ ራሱን በደለኛ ያደርጋል። ከዚህ ይልቅ አቅምና ችሎታው በሚፈቅድለት መጠን ቢንቀሳቀስ ኖሮ ያሰበው ግብ ላይ መድረስ በቻለ ነበር፤ ከዚያ የሚገኘው እርካታ ተጠቃሚም በሆነ ነበር።

ሰዎች ላይ በጐ ተጽዕኖ ማሳደር የሚቻለው መጀመሪያ እኛ ላይ እምነት ሲኖራቸው ነው፤ የሌሎችን እምነትና ከበሬታ ማጣት ብዙ መሪዎችን ከባድ ዋጋ አስከፍሎአል።

6

መሪነትን በተመለከተ ጳውሎስ የሰጠው መመሪያ

እንግዲህ ኤጲስ ቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል፤ የማይነቀፍ፣ የአንዲት ሚስት ባል፣ ልከኛ፣ ራሱን የሚገዛ እንደሚገባው የሚሠራ፣ እንግዳ ተቀባይ፣ ለማስተማር የሚበቃ፣ የማይሰክር፣ የማይጨቃጨቅ፣ ነገር ግን ገር የሆነ፣ የማይከራከር፣ ገንዘብን የማይወድ፣ ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር፣ ሰው ግን የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ይጠብቃታል? በትዕቢት ተነፍቶ በዲያብሎስ ፍርድ እንዳይወድቅ አዲስ ክርስቲያን አይሁን። በዲያብሎስ ነቀፋና ወጥመድም እንዳይወድቅ፣ በውጭ ካሉት ሰዎች ደግሞ መልካም ምስክር ሊኖረው ይገባዋል።

1ኛ ጢሞቴዎስ 3:2-7።

አንድ ቀን የዚህ ጸሐፊ የቅርብ ጓደኛ የሆነ ሰው «ለመሆኑ የራስህን ድክመትና በደል ሌላው ላይ ስትመለከት በራስህ እንድታፍር አያደርግህም!» ብሎት እንደነበር ያስታውሳል። አንዳንድ ጊዜ መንፈሳዊ ነገሮችን በበለጠ ሁኔታ መረዳት የምንችለው በቃላት ሳይሆን በሌሎች ሕይወት ምሳሌነት ስንመለከታቸው ነው። ለውጤታማ መንፈሳዊ መሪነት ያበቃሉ በማለት የዘረዘራቸው ባሕርያት ከራሱ ከሐዋርያው ጳውሎስ ሕይወት ምሳሌነት መመልከት ይቻላል።

ከታላላቅ መሪዎች የምንመለከተው አንድ የጋራ ባሕርይ ማንነታቸውን ማዳበር የቻሉት በጊዜ ሂደት መሆኑ ነው። የጳውሎስን ሕይወት ይበልጥ በመረመርን መጠን በሁሉም ማለት ሞራላዊም ሆነ በመንፈሳዊ የሕይወት አቅጣጫው ልቆ እናያለን። ስለሆነም ኤ.ደብሊዩ ቶዘር የተሳካ ክርስትና ሕይወትን ከኖሩ የዓለማችን ታላላቅ ሰዎች ዋነኛው ቢያደርጉት የሚያስገርም አይደለም። አደገኛ የቤተ ክርስቲያን ጠላት የነበረውን ሰው ታላቅ መሪና የክርስትና እምነት ተከራካሪ እንዲሆን እግዚአብሔር መምረጡ በጣም ይገርማል! በእርግጥም ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን ካፈራቻቸው ምርጥ መሪዎች አንዱና ዋናው ነበር።

ታላላቅ የመንግሥት ባለሥልጣናት፣ ነገሥታትና የካህናት መሪዎች፣ ወይም በወንዶችም ሆነ በሴቶች ፊት ቆሞ ማገልገል ለጳውሎስ ምንም ልዩነት አልነበረውም። የክርስትና እምነትን በተመለከተ ከፈላስፎች፣ ከሃይማኖት መሪዎችና ከጣዖት አምላኪዎች ጋር ሲከራከር አፍ የማስያዝ ብቃት ነበረው።

ከሰባቱ የአይሁድ ምሑራን አንዱ እንደሆነ በሚታሰበው በገማልያል እግር ሥር ቁጭ ብሎ መማሩ ጥልቅ የብሉይ ኪዳን ዕውቀት እንዲኖረው አስችሎታል። ይህን በተመለከተ ስለ ራሱ ሲናገርም «ለአባቶቼም ወግ ከመጠን ይልቅ እየቀናሁ፣ በወገኔ ዘንድ በዘመኔ ካሉት ብዙዎችን በአይሁድ ሥርዓት እበልጥ ነበር» ብሎአል (ገላ. 1:14)።

አገልግሎቱ ክርስቶስን ማዕከል ያደረገና ለእርሱም ባለው ፍቅር የነደደ ነበር፤ ለክርስቶስ ከነበረው ፍቅር የተነሣም ሊያመልጠው የማይችል ኀላፊነት እስረኛ ሆኖአል። (ሮሜ 1:14፤ 2ኛ ቆሮ. 5:14)። ዘርንና ባሕላዊ ልዩነትን ግምት ውስጥ ባለማስገባት ሰዎችን ሁሉ በወንጌል የመድረስ ሸክም ነበረበት። ሀብታሞችንና ድሆችን፣ የተማሩትንና ያልተማሩትን በእኩል ዓይን ይመለከት ነበር።

ታዲያ፣ እነዚህን ነገሮች መሠረት እስካደረገ ድረስ መንፈሳዊ መሪ ለመሆን ከጳውሎስ የተሻለ መስፈርቱን ያሟላ ማን ሊሆን ይችላል? በነበረው ሰፊ የሕይወት ተሞክሮ ላይ መንፈስ ቅዱስ በሚሰጠው መገለጥ ይደገፍ ነበር። መንፈሳዊ መስፈርቶች በጊዜና በሁኔታዎች የሚለዋወጡ አይደሉም፤ ያኔ የነበሩ መመሪያዎች ዛሬም ቢሆን ያገለግላሉ። እነዚህ ጳውሎስ ተግባር ላይ ያዋላቸው መመሪያዎች ስንፈልግ የምንጠቀምባቸው፣ ሳንፈልግ ደግሞ የምንተዋቸው ሳይሆኑ ምን ጊዜም ቋሚ መስፈርት ናቸው።

እዚህ ላይ *ሌጺስ ቆጶስ* እና *ሽማግሌ* የሚሉት ሁለት ቃላት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድ ዓይነት ሥራ ለሚሠራ ሰው የተሰጡ ስያሜዎች ናቸው። ሽማግሌ የሚለው ክብሩንና ሥልጣኑን ሲያመለክት፣ ኤጶስ ቆጶስ የሚለው ደግሞ ሥራውንና አገልግሎቱን ያመለክታል። በሌላ አነጋገር አንደኛው ሰውየውን፣ ሁለተኛው ደግሞ ሥራውን ያመለክታል ማለት ነው። ለዚህ አባባላችን መሠረት የሚሆነን አሳብ የምናገኘው ከሐዋርያት ሥራ 20:17 እና 28 ሲሆን አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ ሥራ ያላቸውን ሰዎች የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችና ጳጳሳት በማለት ሲጠራቸው እንመለከታለን።

በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ የተመለከትነው ጥቅስ አንድ መሪ በተለያየ የሕይወት ገጽታውና ማኅበረ ሰባዊ ግንኙነቱ ሚሚላት የሚገቡትን መስፈርቶች ይዘረዝራል።

ማኅበረ ሰባዊ መስፈርቶች

አንድ መሪ በቤተ ክርስቲያን ባሉ ሰዎች ዘንድ *የማይነቀፍ* መሆን አለበት። ጸባዩም ሆነ ዝንባሌው ለነቀፋና ለትችት የሚያጋልጠው ሆኖ እንዳይገኝ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅበታል። በዚህ ሁኔታ ሐሜተኞችና ወሬ አመላላሾች ለአሉባልታና ስም ማጥፋት ምክንያት የሚሆናቸውን ነገር ማግኘት የለባቸውም። ምናልባት በክፉ የሚያነሱትና ስሙን የሚያጠፉ ሰዎች ቢኖሩ እንኳ፣ አኗኗሩ፡ ስም አጥፊዎችን የሚሳፍርና ሰበብ የሚያሳጣ መሆን አለበት።

ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ባሉ ሰዎች ዘንድ ደግሞ *መልካም ምስክር* ሊኖረው ይገባል። ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ባሉ የሥራ እንቅስቃሴዎች ከክርስቲያን ጋር የሚውል ሰው ስለዚያ ወንድም ጸባይ ምስክር ሊሆን ይችላል። ጳውሎስ ይህን መስፈርት ያስቀመጠበት ምክንያት በጣም ግልጽ ነው። የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ የሚያውቀው አንድ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ብዙ ሰዎችን ቀጥሮ የሚያሠራበት አንድ ትልቅ መሥሪያ ቤት ነበረው። የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ እንደመሆኑ መጠን አንዳንድ ጊዜ እሑድ መልእክት እንዲያቀርብ ይጋበዝ ነበር። ታዲያ፣ አብረውት የሚሠሩ ሰዎች «እሑድ ዕለት መስበክ አለ መስበኩን በትክክል እናውቃለን፤ ምክንያቱም እሑድ ዕለት ከሰበከ ሰኞ ባልተለመደ ሁኔታ በትንሽ በትልቁ ሲቆጣ ስለምናየው ነው» ይሉ ነበር። ይህ ሰው አብረውት ለሚሠሩ ሰዎች እውነተኛ የክርስቶስ ምስክር መሆን አልቻለም ማለት ነው።

ምንም እንኳ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች የተለያየ ነቀፋና ትችት ቢኖራቸውም አጠቃላይ በሆነ መልኩ ለክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር አክብሮት አላቸው፤ ይህን ክርስቲያናዊ ምግባር በአንድ ሰው ሕይወት ሲመለከቱ «ምነው እንደ እርሱ ያለ ሕይወት በነበረኝ!» የሚል ምኞት ያድርባቸዋል። በዚያ ሰው ላይ ለነቀፋና ለትችት ምክንያት የሚሆናቸው ተጨባጭ ምክንያት አይኖራቸውም። አንድ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ የሆነ ሰው አማኝ ባልሆኑ ሰዎች ዘንድ እንኳ የተከበረና እምነታቸውን የሚጥሉበት ዓይነት መሆን አለበት የተባለው በዚህ ምክንያት ነው። እነርሱም ክርስቲያን እንዲሆኑ ፈቃድና ዝንባሌያቸውን ማነሣሣት የሚችል መሆን አለበት። ምሉሉነት ያለው ሕይወት በአንደበታችን ከምንናገረው ቃል የበለጠ ኃይል አለው።

ሥነ ምግባራዊ መስፈርቶች

ሞራላዊ እሴቶችና መስፈርቶች ለጥቃት በተጋለጡበት ዓለም አንድ አገልጋይ ይህን በተመለከተ የማይነቀፍ ሆኖ ሊገኝ ይገባል። የአከባቢው ልማድና አኗኗር ከዚህ የሚጻረር ቢሆን እንኳ *«የአንዲት ሚስት ባል»* መሆን አለበት። ይህን በተመለከተ የተለያየ አተረጓጐምና ፍቺ መኖሩ ቢታወቅም በዚህም ሆነ በዚያ ሞራላዊ ሕይወቱ ያለ ነቀፋ ሊሆን ይገባል። ለምትኖረው አንዲትና ብቸኛ የትዳር ጓደኛ ታማኝና በምንም ዓይነት ሁኔታ የማይነቀፍ መሆን አለበት።

ልከኛ መሆን አለበት ። ይህ ብዙ ነገሮችን የሚመለከት ቢሆንም የመጠጥ ሱሰኛ ያልሆነ የሚለው በዚሁ ውስጥ መካተት ይችላል። ጠጪ ሰው መስከሩ የማይቀር ነው፤ ከሰከረ ደግሞ ከሥርዓት ይወጣል። ጠጪ ሰው ሌላው ቀርቶ በማኅበረ ሰቡ ዘንድ እንኳ ክበሬታ የለውም፤ እንደዚያ ከሆነ ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን ያህል ዝቅተኛና ወራዳ ስፍራ እንደሚያሰጠው ግልጽ ነው። አንድ አገልጋይ ከሰዎች ተደብቆ የሚለማደው ምንም ነገር ሊኖረው አይገባም፤ በስውር የሚለማመደው ኃጢአት በግልጽ መውጣቱ አይቀርም፤ ክርስቲያናዊ ምስክርነቱንም ያበላሽበታል።

አእምሮአዊ መስፈርቶች

ራሱን የሚገዛ መሆን አለበት። በሚያደርገው ሁሉ ሚዛናዊነትን የጠበቀ፤ በሥርዓትና በማስተዋል የሚመላለስ ሊሆን ይገባል። ይህም በውስጡ ያለውን ራስን የመቆጣጠር ችሎታና ሚዛናዊነትን ይመለከታል። አንድ ሰው ስለዚህ ጉዳይ ሲናገሩ፤ «አእምሮን የምንገራበት፤ ምኞትን የምንገታበት ልጓም» ብለዋል። ለእንዲህ ዓይነቱ ችሎታ ግሪኮች ከፍተኛ ግምት ይሰጡ ነበር። ግሪኮች ቃሉን የሚረዱት «በትንሽ በትልቁ የማይናወጥ፤ በስሜት ተነሣሥቶ አንድን ነገር የማያደርግ፤ በአመለካከትና በአስተሳሰቡ ጽንፈኛ ያልሆነ፤ ይልቁንም በነገር ሁሉ የተረጋጋና ራሱን የሚገዛ አእምሮ ያለው» በሚለው መልኩ ነው። አንድ መሪ ራሱን መግዛት ከቻለ በሌላ የሕይወት ገጽታዎቹም ቢሆን ሚዛናዊነትን የጠበቀ ሊሆን ይችላል።

ውጫዊ የሕይወት ገጽታውን በተመለከተም ***የተከበረና በሥርዓት የሚመላለስ*** መሆን ይጠበቅበታል። ሥርዓታማ ሕይወት የሥርዓታማ አስተሳሰብ ወይም አእምሮ ውጤት ነው። ምስቅልቅል ነገርን ማስተካከልና ሥርዓት ማስያዝ የእግዚአብሔር ዓይነተኛ ባሕርይ ነው፤ ይህ ባሕርይ ደግሞ መሪው በሚኖረው ሥርዓት ያለው ሕይወት

መታየት አለበት። በዕውቀቱም ሆነ በሚኖረው መንፈሳዊ ሕይወት ለማስተማር የሚበቃ መሆን አለበት። ለማስተማር የሚበቃ ሲል ችሎታን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን በቅዱሳት መጻሕፍት አማካይነት መንፈስ ቅዱስ የሚገልጥለትን እውነት ለሌሎች ለማካፈል እንዲችል ምንጊዜም ዝግጁ ሆኖ መገኘትን ያመለክታል። ሌሎችን ለማስተማር የሚበቃው ደግሞ እርሱ ራሱ ከቅዱሳት መጻሕፍት የተማረ ሲሆን ነው። ውጤት ባለውና ፍሬያማ በሆነ ሁኔታ ሌሎችን ማስተማር የማይችል ሰው መንፈሳዊ መሪ ሊሆን አይገባም። መንፈሳዊ መሪ በብዙም ይሁን በጥቂቱ ከበታቹ ያሉትን ሰዎች የማስተማር ኃላፊነት አለበት፤ ትምህርቱም ከነቀፋ በላይ በሆነ ሕይወቱ መደገፍ ይኖርበታል።

ሳሙኤል ብሬንግል የተባሉ ሰው

> አንድ ጥሩ ሐኪም የሕመምተኞቹን ሁኔታ በሚገባ ተረድቶ አስፈላጊውን መድኃኒት እንደሚያዝዝ ሁሉ የሰዎችን ችግርና ጥልቅ መሻት በመረዳት እውነትን ማቅረብ የሚችሉ መምህራንና መሪዎች በመካከላችን መኖራቸው ምን ያህል አስፈላጊ ይሆን? የሰዎች ነፍስ ታማሚ ናት፤ ሕመሙ ግልጽ ወይም ስውር ሊሆን ይችላል፤ ሥር የሰደደ ወይም ጊዜያዊ ሊሆን ይችላል፤ ያም ሆነ ይህ በኢየሱስ ያለው እውነት ብቻ መፈወስ የሚችለው ደዌ እንዳለባቸው ግን ግልጽ ነው። አንድ ሐኪም ለበሽተኞች አንድ ዓይነት መድኃኒት እንደማያዝዝ ሁሉ፣ ለሰዎች የተለያየ ችግር የምናቀርበው እውነትም እንዲሁ ሊለያይ ይችላል። ቃሉን በትጋት ማጥናትና አስፈላጊውን መገለጥ መንፈስ ቅዱስ እንዲሰጠን አጥብቀን መጸለይ ያለብንም በዚህ ምክንያት ነው በማለት ተናግረዋል።

ጆን ዌስሊ በከፍተኛ ደረጃ እነዚህን መስፈርቶች ያሟላ አገልጋይ ነበር። የሰዎችን አእምሮአዊ እውቀት አያንቋሸሸም፣ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ሞራላዊና መንፈሳዊ ሕይወታቸውንም እንዲሁ ለማሳደግ ይጥር ነበር። ራሱ ጆን ዌስሊ በጣም የተማረ ከመሆኑም በላይ ወደዚያ ቢያዘነብል ኖሮ በዘመኑ ከነበሩ ታላላቅ ምሑራን አንዱ ለመሆን ይችል እንደነበር ይነገራል። አያሌ መጻሕፍትን መርምሮአል፤ ከፍተኛ የሥነ ጽሑፍ እውቀትም ነበረው፣ አንድ በዘመኑ የነበረ ታዋቂ ሰባኪ ስለ ጆን ዌስሊ ሲናገር- «ሥነ ጽሑፍንና ጠቅላላ እወቀትን አቀነባብሮ የያዘ የጆን ዌስሊ ስብከትን የመሰለ ስብከት ፍጹም ሰምቼ አላውቅም» ብሎአል። ያም ሆኖ ግን ዌስሊ ይበልጥ የሚታወቀው «የአንድ መጽሐፍ ሰው» ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ሰው በሚለው መለያው

ነበር። አንጸባራቂ ምሳሌነት ያለው ሕይወትና የተቀደሰ አእምሮ ያለው አገልጋይ ነበር።

ሰብዕናን የሚመለከቱ መስፈርቶች

ክርስቲያን መሪ በነገር ሁሉ ረጋ ያለና ጭምት እንጂ *ጨቅጫቃ* መሆን የለበትም፤ በሚያደርገው ሁሉ ምክንያታዊና ከሰዎች ጋር ተጣጥሞ መሥራትን መቻል ይኖርበታል። አሪስቶትል የተባለ የግሪክ ፈላስፋ እንደሚለው መሪ ለመሆን የሚበቃ ሰው «ከክፉ ይልቅ መልካሙን፣ እርሱ ያደረገውን ሳይሆን፣ ሌሎች ለእርሱ ያደረጉለትን መልካም ነገር ያስባል።» ነገሮችን በቸልታ ከማለፍ ይልቅ ለአስቸጋሪ ሁኔታዎች ሁሉ ለላማዊ መፍትሔ ይፈልግላቸዋል።

በተጨማሪም *እንግዳ ተቀባይና* ባይተዋሮችን ማስተናገድ የሚችል ሰው መሆን አለበት። እንግዶችን የመቀበልና የማስተናገድ አገልግሎቱን ጌታን ለማገልገል እንዳደረገው ተግባር እንጂ የሚያነጫንጨው መሆን የለበትም። ምንጊዜም የቤቱ በር ለእግዚአብሔር አገልጋዮች ክፍት መሆን ይኖርበታል።

እንግዶችን ስለ መቀበል ጳውሎስ ይህን በጻፈበት ጊዜ ከአሁኑ ዘመን ይልቅ እጅግ አስፈላጊ አገልግሎት ነበር። ያም ሆኖ ግን ዛሬም ቢሆን ከአንድ አገልጋይና ሚስቱ የሚጠበቅ ተግባር ነው። እንግዶችን የመቀበል አገልግሎት አብዛኛው ጫና የሚያርፈው ከአገልጋዩ ይልቅ በሚስቱ ላይ እንደሚሆን ይታወቃል። በጥንት ቤተ ክርስቲያን ዘመን ሆቴሎች በጣም ጥቂት ነበሩ፤ በዚህ ላይ ደግሞ የቆሸሹና ለርኩሰት መፈጸሚያ የሚጠቀሙባቸው ነበሩ። አረማውያን ወይም ወንጌልን ያልተቀበሉ ሰዎች ክርስቲያኖችን ወይም ከአገር አገር እየተዘዋወሩ የሚያስተምሩ መምህራንን በቤታቸው ተቀብለው ለማስተናገድ ፈቃደኛ አልነበሩም። በተለያዩ መልኩ ብርቱ ስደት ነበር፤ ለሀገሩ ባዕድ የሆኑ ክርስቲያኖች እየታደኑ እንደ ባሪያ የሚሸጡበት ዘመን ነበር። ስለሆነም ይህ ኃላፊነት የእያንዳንዱ ክርስቲያን በተለይም ደግሞ የአገልጋዮች መሆን ነበረበት። ክርስቲያኖችንም ሆነ ክርስቲያን ያልሆኑትን ለመቀበልና ለማስተናገድ ምን ጊዜም ፈቃደኛ ሊሆኑ ይገባል።

የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ ከፍተኛ ኃላፊነት የነበረውና በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ጉቁ ተሳትፎ የሚያደርግ ጓደኛ ነበረው። ይህ ሰው እንግዶችን ተቀብሎ ለማስተናገድ ምን ጊዜም በሩ ክፍት ነበር። በዚህ አገልግሎቱ የመንፈሳዊ መሪነት ችሎታው እጅግ ማደግ ከመቻሉም በላይ የግል ሕይወቱም ተባርኮአል፤ ለሌሎችም በረከት መሆን ችሎአል።

ስግብግብነትና ገንዘብን መውደድ ከአንድ መንፈሳዊ መሪ የማይጠበቁ ባሕርያት ናቸው። አንድ መንፈሳዊ አገልጋይ በምንም ዓይነት ገንዘብን ወይም ጥቅማ ጥቅምን ለማግኘት መሥራት የለበትም። ጥቅም የሚያስገኘውንም ሆነ ጥቅም የማያስገኘውን ኃላፊነት በእኩል ሚዛን ይቀበላል።

ጆን ዌስሊ ማዴሊ በሚባል ስፍራ ያገለግል ስለነበር ፍሌቸር ስለሚባል አገልጋይ ሲናገር እንዲህ ብሎ ነበር - «በአውሮፓም ሆነ በአሜሪካ ዞሬአለሁ እርሱን የሚመስል ያለ ነቀፋ የሆነ ሕይወት ያለውን ሰው ግን በፍጹም አላገኘሁም።» ማዴሊ ወደ ሚባለው ስፍራ ሄዶ ማገልገል ከመጀመሩ በፊት አንድ ሰው «ወደ ዱንሃም መጥተህ ብታገለግል መልካም ይመስለኛል፤ ምክንያቱም የሰበካው ጉባዔ አባሎች ጥቂት ናቸው። ሥራው ቀላል ነው። ደመወዙ ግን ብዙ ነው አካባቢው ለጤና ተስማሚና መዝናናት የምትችልበት ነው» በማለት ላቀረበለት ግብዣ ፍሌቸር ሲመልስ፡- «ዱንሃም ለእኔ ተስማሚ አይደለም። ምክንያቱም ሥራው አንሶአል፤ ገንዘቡ ግን በዝቶአል» ነበር ያለው። ግብዣ አቅራቢውም ባገኘው መልስ ቅር በመሰኘት ፡- «እንዲህ ያለውን አጋጣሚ አለመቀበል ያሳዝናል፤ ሌላ ምን ላደርግልህ እንደምችልም አላውቅም፤ ለመሆኑ ማዴሊ ወደሚባል ስፍራ ሄደህ ለማገልገል ፈቃደኛ ነህ?» በማለት ለቀረበለት አማራጭ «አዎን ወደዚያ ሄጄ ማገልገልን ነው የምፈልገው» በማለት ይመልሳል። ግብዣውን ያቀረበለት ሰው «የእኔ ዓላማ ወደሚስማማህ ስፍራ ሄደህ እንድታገለግል በመሆኑ ምርጫህ ማዴሊ እስከሆነ ድረስ እዚያ ያለውን አገልጋይ እጥፍ ጥቅም ወደሚያገኝበት ወደ ዱንሃም ማዛወር አይከብደኝም» አለ።

ይህ ሰው ምንም ዓይነት ስግብግብነትና ገንዘብ ወዳድነት ባልነበረበት ትንሽ ቤተ ክርስቲያን በከፍተኛ ደረጃ እግዚአብሔርን ከማገልገሉም በላይ የሕይወትን ታሪኩን በማንበብም ሰዎች እስከ ዛሬ ድረስ እየተባረኩ ነው።

የቤተሰብ ሕይወትን የሚመለከት መስፈርት

ባለትዳር የሆነ ክርስቲያን መሪ ቤተሰቡን በመንፈሳዊ መንገድ የማስተዳደር ችሎታቸውን ማስመስከር ይኖርበታል። «ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር» ሊሆን ይገባል። ብዙ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች የመሪነት ችሎታ ጥያቄ ውስጥ የወደቀው ቤተሰብን በተመለከተ የማስተዳደር ብቃት ስለጐደላቸው እንደሆነ መቀበል ይከብዳቸኋልን? እያስተዳደረ

ወይም እየገዛ ሲል ፍጹም ነጻነት በሚያሳጣ ሁኔታ እየጨቆነ ማለት አይደለም፤ «በመልካም የሚያስተዳድር» የሚለው ቃል የሚያመለክተው ተገቢው አክብሮትና ፍቅር ሳይነፈጋቸው መሆኑን ነው።

ይህን በተመለከተ አገልጋዩ እንዲሳካለት ከተፈለገ መንፈሳዊ ራእዩን የምትጋራውና አስፈላጊ ከሆነም ማንኛውንም መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ የሆነች ሚስት ልትኖረው ይገባል። ትክክለኛ ሚስት ባለ መምረጣቸው ብዙ ስጦታዎች የነበሩዋቸው አገልጋዮች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ውጤታማ መሆን አልቻሉም። አንድ ሰው የራሱን ቤተሰብ በአግባቡ መምራትና ማስተዳደር ካልቻለ፣ የእግዚአብሔርን ቤተሰብ በአግባቡ ማስተዳደር የሚችል ይመስላችኋል? የራሱን ቤት ማስተዳደር ካልቻለ፣ የራሱንም ልጆች በአግባቡ መምራት ካልቻለ፣ የሚፈልገውን ያህል እንግዶችን በቤቱ ማስተናገድ አይችልም፤ የራሱን ቤተሰብ መለወጥ ያልቻለ ሌሎች ቤተሰቦችን መለወጥ ይችላል ማለት የማይታሰብ ነው።

እዚህ ላይ ያለው አንድምታ አንድ ሰው የቱንም ያህል በቤተ ክርስቲያን ሆነ በሌሎች መንፈሳዊ ጉዳዮች ተሳትፎ ቢያደርግም የራሱን ቤተሰብ ችላ ማለት የለበትም፤ ምክንያቱም ዋናውና ትልቁ ኃላፊነቱ በመጀመሪያ ደረጃ የራሱን ቤተሰብ ማስተዳደር ነው። በእግዚአብሔር አሠራር መሠረት እርሱ የሰጠንን ኃላፊነት መወጣት ማለት ሌላው ኃላፊነታችንን ግን መበደል ማለት አይደለም። በእያንዳንዱ የሕይወት ገጽታችን ማንኛውንም ኃላፊነታችንን አሟልተን መገኘት አለብን። ጳውሎስ እንደሚነግረን አንድ ሰው በሌሎች ላይ መንፈሳዊ ሥልጣን የሚኖረው በመጀመሪያ ደረጃ የራሱን ቤተሰብ በፍቅርና በጥበብ ማስተዳደር ሲችል ነው። በቤተሰቡ ያልተሳካለት መሪ በሌላው ዘርፍም እንዲሁ ሊሳካለት አይችልም።

በሳልና አስተዋይ መሆን ይጠበቅባቸዋል

መንፈሳዊ ብስለት ለመልካም መሪነት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፤ ሁለቱ በፍጹም አይነጣጠሉም። ስለ ሆነም አዲስ ጀማሪ ወደ ም በቅርቡ ጌታን ለተቀበለ አማኝ መንፈሳዊ ኃላፊነት ሊሰጠው አይገባም። እዚህ ላይ አዲስ የሚለው ቃል በግሪክኛው መሠረት የሚያመለክተው «በቅርቡ የተተከለ» ችግኝን ሲሆን ምሳሌው ተፈጥሮን መሠረት ያደረገ ነው። አንድ ችግኝ ሥር እንዲሰድና እንዲያድግ ጊዜ ያስፈልገዋል፤ ይህን ሂደት ማቻኮል ወይም ማፋጠን አይቻልም። ከላይ በኩል ፍሬው ከመታየቱ በፊት ከታች በኩል ሥሩን መስደድ አለበት። ከዚህ ምሳሌ

ጋር በሚስማማ ሁኔታ ቤንግል አዲስ ክርስቲያንን በተመለከተ ሲናገር «አዲሱ ክርስቲያን መራራጥና ላይ ታች ማለትን ያበዛ ይሆናል፤ ይሁን እንጂ የመስቀሉ የመገረዝ ኃይል ገና በሕይወቱ አላለፈም» ብሎአል። በ1ኛ ጢሞቴዎስ 3:10 ጳውሎስ ዲያቆናት ማሟላት ስለሚገባቸው መስፈርት ሲዘረዝር «እነዚህም ደግሞ አስቀድመው ይፈተኑ» ብሎአል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለኃላፊነት ሥልጣን ብቁ መሆን አለመሆናቸው የሚለካው በዚህ ነው።

ጢሞቴዎስ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን መጋቢ በሆነ ጊዜ ያ ቤተ ክርስቲያን ከአሥር ዓመት የሚበልጥ ዕድሜ ነበረው። እውቅ መጋቢዎችና መምህራን የነበሩበት እንደመሆኑ መጠን በሳሎችና ሰፊ የሕይወት ልምምድ ያላቸው ሰዎችም ነበሩበት። ስለሆነም መሪዎች ይህን ባሕርይ አሟልተው መገኘት እንደሚገባቸው መናገሩ ያለ ምክንያት አልነበረም። በሚስዮናዊ አገልግሎትና አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን በማሳደግ ረገድ ጳውሎስ ሰፊ ተሞክሮ ነበረው፤ ስለ ሆነም እንዲህ ያሉ ሰዎችን በቀላሉ ማግኘት እንደማይቻል ስለሚያውቅ አዳዲሶቹ አብያተ ክርስቲያናት እነዚህን መስፈርቶች እንዲያሟሉ አይጠበቅባቸውም ነበር። (ቲቶ 1:5-9) ገና በማደግ ላይ ካሉ አብያተ ክርስቲያናት ብዙ አይጠበቅባቸውም፤ ይሁን እንጂ ለመሪነት የሚታጩ ሁሉ በባሕርያቸው ረጋ ያሉ፣ በአመለካከታቸው መንፈሳዊ የሆኑና ለሥልጣንና ለደረጃ ጉጉት የሌላቸው እንዲሆኑ ይገባ ነበር።

አዲስ ክርስቲያን መሪ መሆን የለበትም በማለት የተናገረበትን ምክንያት ጳውሎስ ሲገልጽ «በትዕቢት ተነፍቶ በዲያብሎስ ፍርድ እንዳይወድቅ አዲስ ክርስቲያን አይሁን» ይላል። አዲስ ክርስቲያን ለመሪነት ብቁ የሚያደርው መንፈሳዊ ብስለትና የሰከነ ሕይወት ይጐድለዋል። የተለያየ ችሎታ ቢኖራቸውም ለአዳዲስ ክርስቲያኖች ቁልፍ ቦታዎችን መስጠት የሚደገፍ አይደለም፤ እንዲህ ያለ ሹመት ለቤተ ክርስቲያንም ሆነ ለተሿሚው አይጠቅምም። የሰው ተፈጥሮ ምን ጊዜም ቢሆን ያው በመሆኑ አዲሱ ክርስቲያንም ከጓደኞቹ ይልቅ ለዚህ ትልቅ ኃላፊነት ቢመረጥ እኔ በጣም አስፈላጊ ስለሆንሁ ነው በማለት መታበይ ይጀምራል። ይሁን እንጂ ምንም እንኳ በችኮላ ትልቅ የኃላፊነት ስፍራ ባይሰጠውም ተስፋ የሚጣልበት ሆኖ እስከተገኘ ድረስ አንዳንድ ዝቅተኛ ሥራዎች ሊሰጡት ይገባል፤ በዚህ ሁኔታ ተፈጥሮአዊና መንፈሳዊ ስጦታዎቹን ማዳበር ይችላል። በትዕቢት ተነፍቶ ችግር ላይ እንዳይወድቅ በፍጥነት እድገት ማግኘት የለበትም። ተስፋ እንዳይቆርጥም የማያስፈልግ ጫና ሊደረግበት አይገባም።

ይህን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ዊልያም ሔንድሪክሰን እንደሚነገሩን በመጀመሪያው ሐዋርያዊ ጉዞው በሄደበት ቦታ ሁሉ ጳውሎስ ማንንም ለቤተ ክርስቲያን መሪነት አልሾመም፤ እነዚያን አብያተ ክርስቲያናት በድጋሚ በጐበኘት ጊዜ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው አድገውና ጉልምሰው ያገኛቸው ነበር። ለዚህ ኃላፊነት የሾመው ጢሞቴዎስም ቢሆን በጌታ እንዳመነ ወዲያውኑ ለመጋቢነት አልተሾመም (የሐዋ. 14፡23)። በጌታ ያመነው በመጀሪያው የጳውሎስ ሐዋርያዊ ጉዞው ቢሆንም ለመጋቢነት የተመረጠው ግን ሁለተኛውን ሐዋርያዊ ጉዞ ባደረገ ጊዜ ነበር።

መንፈሳዊ ብስለት የሚንጸባረቀው በመንፈሳዊ ሕይወት ለጋስነትና አመለካከት ስፋት ነው። ፊት ለፊት ከክርስቶስ ጋር መገናኘቱ ጳውሎስን ከነበረበት ጠባብ አመለካከት አውጥቶ ሰዎችን ሁሉ የሚቀበል ባለ ሰፊ አእምሮ አድርጎታል። በውስጡ የሚኖረው ክርስቶስ ልበ ሰፊ አደረገው፤ የአመለካከት አድማሱንም አሰፋለት። ይሁን እንጂ እይታና አመለካከቱ ቢሰፋም በገርነት የተቀበለውን እምነት እንዲክድ አላደረገውም።

ክርስቲያን መሪዎችን በተመለከተ ከላይ የተመለከትናቸው መስፈርቶች ለዓለማውያን መሪዎች እንኳ ቢሆን በጣም አስፈላጊ ናቸው። በጥንት ዘመን የነበረ አንድ አረማዊ ጸሐፊ አንድ የጦር መሪ ምን ዓይነት ሰው መሆን እንደሚገባው የጻፈውን ዊልያም ባርክሌይ እንደሀ በማለት አስቀምጠዋል፦ «በከፍተኛ ደረጃ ራሱን የሚገዛና ልከኛ መሆን አለበት፤ በፍጹም ብኩንና ዝርክርክ መሆን የለበትም። ለመከራና ለችግር እጁን የማይሰጥ፤ የሚቻል ከሆነ የቤተሰብ ኃላፊ የሆነ፤ ተናግሮ የማሳመን ችሎታና በሰዎች ዘንድ ከበሬታ ያለው ሊሆን ይገባል።» አባባሉ ጳውሎስ ካቀረበው ዝርዝር ጋር ተመሳሳይ መሆኑ በጣም የሚገርም ነው። እንግዲህ ዓለም ከመሪዎቹ ይህን የመሰለ መስፈርት የሚጠብቅ ከሆነ፣ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ከሚያስተዳድሩ መሪዎችስ ከዚህ ያነሰ የሚጠበቅባቸው ይመስላችኋል?

7

መሪነትን በተመለከተ ጴጥሮስ ያቀረበው መመሪያ



እንግዲህ እኔ፣ ከእነርሱ ጋር ሽማግሌ የክርስቶስም መከራ ምስክር ደግሞም ሊገለጥ ካለው ክብር ተካፋይ የሆንሁ በመካከላቸው ያሉትን ሽማግሌዎች እመክራቸዋለሁ፤ በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፣ በበጉ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጕብኙት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብርን አክሊል ትቀበላላችሁ። እንዲሁም ጕበዞች ሆይ፣ ለሽማግሌዎች ተገዙ፤ ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ፣ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና፣ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል። እንግዲህ በጊዜው ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከኃይለኛው ከእግዚአብሔር እጅ በታች ራሳችሁን አዋርዱ፤ እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት።

1ኛ ጴጥሮስ 5፡1-7

ጴጥሮስ በሐዋርያቱ መካከል ተቀባይነት ያገኘ መሪ ነበር። እርሱ ያደረገውን ሌሎችም ያደርጋሉ። እርሱ ወደሄደበት ሌሎችም ይሄዳሉ። «ዓሣ ለማጥመድ እሄዳለሁ» ሲል «እኛም ከአንተ ጋር እንሄዳለን» ይላሉ። አልፎ አልፎ አንዳንድ ስሕተቶችን መፈጸሙ እውነት ቢሆንም አብረውት በነበሩ ላይ ያለው ተጽዕኖ ቀላል አልነበረም፤ የመሪነት ኃላፊነቱንም የሚጋፋ አልነበረም። ከብዙ ዓመታት ልምዱ በመነሣት ለመንፈሳዊ መሪዎች የጻፈውን ምክር በአንክሮ ማስተዋል በጣም ይጠቅማል። የጻፈው በስደት ላይ የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን በመምራት ላይ ላሉ ሰዎች ቢሆንም ጊዜ የማይሽረው ምክሩ በየትኛውም ዘመን፣ በየትኛውም የመሪነት ደረጃ ላሉ ሰዎችም ይጠቅማል።

የመጀመሪያውና ዋናው ኃላፊነት ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን መንጋ በጥንቃቄ መምራት እንደሆነ ከብዙ ዘመናት እረኝነት ተሞክሮ

ሲናገር፡፡ «የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ» ይላል (5:2)፡፡ ጴጥሮስ በአንድ ወቅት ታላቅ ስሕተት ፈጽሞ እንደነበር ይታወሳል፤ ይሁን እንጂ ከዚያ በኋላ ከጌታ ጋር ያደረገውን የአሳብ ልውውጥ በፍጹም አይዘነጋውም (ዮሐ. 21:15-17)፡፡ እንዲያውም ከላይ የተመለከትነው ቃል የዚያ ወቅት ተሞክሮን የሚያስታውስ ነው ማለት ይቻላል፡፡ እነዚያ «እንግዶችና መጻተኞች» የሚላቸው (1ኛ ጴጥ. 1:1) ሰዎች እያለፉበት ስላለው መከራ ያውቃል፤ ስለሆነም በከፍተኛ ደረጃ ጥበቃና እንክብካቤ ሊደረግላቸው እንደሚገባም ይገነዘባል፡፡ ለቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የሚጽፈውም ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

ጴጥሮስ ይህን የሚጽፈው ራሱን እንደ አለቃ ወይም መሪ በመቁጠር ሳይሆን «ከእናንተ ጋር አብሬ ሽማግሌ የሆንሁ» በሚል መንፈስ እንደነበረ መገንዘብ ይኖርብናል፤ እርሱም ሆነ እነርሱ ያለባቸው ኃላፊነት አንድ ዓይነትና ተመሳሳይ እንደሆነ ያስባል፡፡ ከጐናቸው ሆኖ ምክር እያካፈላቸው እንጂ፣ ከበላይ ሆኖ ትእዛዝ እያስተላለፈ አይደለም፤ ይህም ከአንድ መሪ የሚጠበቅ ባሕርይ ነው፡፡ በማንኛውም ነገር ከእርሱ እኩል እንደሆኑ ያስባል፡፡ ባለፈ ውድቀቱ ልቡ እንደተሰበረ ሆኖም በመስቀሉ ፍቅር የተሰበረ ልቡ እንደተጠገነለት ሰው ሆኖ ነው የሚጽፍላቸው፤ የክርስቶስን መከራ በማስታወስም ይጽፋል፡፡ የእውነተኛ እረኛ ልብ የሌለው ሰው የእረኝነት ተግባሩን በሚገባ መወጣት አይችልም፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ጴጥሮስ አንድ መሪ ሊኖረው ስለሚገባ ዓላማ ያነሣል፡፡ መንፈሳዊ መሪ ኃላፊነቱን መወጣት ያለበት ሌሎችን በመጫን ወይም በማስገደድ መሆን እንደሌለበት ሲያሳስብ «በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤. . .በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን ጕብኙት. . . ማጎበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ» ይላል፡፡ ጴጥሮስ ይህን በጻፈበት ዘመን የነበረው ችግር በጣም ጠንካራ ልብ አለው የሚባለውን ሰው ወኔ እንኳ የሚያላላ ነበር፤ ይሁን እንጂ መሪዎች በዚህ ሁኔታ መደናገጥ እንደሌለባቸው ያሳስባል፡፡ ከነበረው ውጥረት የተነሣ እንዲሁ ኃላፊነትን ለመወጣት ወይም ከግብር ይውጣ ዝንባሌ ሳይሆን በመለኮታዊ ፍቅር ተነሣሥተው ሕዝቡን መምራት እንደሚገባቸው ይመክራል፡፡ አንድ መሪ ኃላፊነቱን መወጣት ያለበት እርሱ በወደደው ወይም ለእርሱ ደስ እንዳሰኘው ሳይሆን «እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ» መሆን አለበት (5:2)፡፡ አንድ ሰው ይህን አስመልክቶ ሲጽፍ፡-

ጴጥሮስ ሕዝቡን «እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ምሩት» ይላል። የእስራኤል ሕዝብ በተለየ መልክ የእግዚአብሔር ዕድል ፈንታ እንደነበር ሁሉ እኛም በኃላፊነት የተሰጠንን ሕዝብ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መምራት አለብን። የእግዚአብሔር ትዕግሥት፣ የእግዚአብሔር ይቅር ባይነትና ፍቅር ሊኖረን ይገባል ይላል።

እግዚአብሔር ኃላፊነትን ሲሰጠን የበቃን አይደለንም፤ ወይም የማንረባ ደካሞች ነን በሚል ዝንባሌ ላለመቀበል ማንገራገር የለብንም። ቀድሞውንስ ቢሆን በራሱ ማንነት ለእንዲህ ዓይነቱ ኃላፊነት ማን ብቃት ሊኖረው ይችላል? እስራኤልን ከግብጽ እንዲያወጣ እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው ጊዜ ሙሴ ያንን ላለመቀበል ብዙ ምክር ነበር፤ ይሁን እንጂ ይህን በማለቱ እግዚአብሔር አዝኖበታል፤ ተቈጥቶታል (ዘጸ. 4:14)።

መንፈሳዊ መሪ ከአገልግሎቱ ጥቅምን ማስቀደም የለበትም፤ «መጥፎውን ረብ በመመኘት» መሆን የለበትም። ሥልጣንን ወይም ጥቅምን ማስቀደም ምን ያህል አደገኛ መሆኑን ጴጥሮስ በአንድ ወቅት የአገልግሎት ጓደኛው ከነበረው ይሁዳ ሕይወት ተምሮአል፤ ስለሆነም የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ወይም መሪዎች ከእንዲህ ዓይነቱ ዝንባሌ ነጻ መሆን እንዳለባቸው ያሳስባል። አንድ መሪ በአገልግሎቱ ወይም በውሳኔው የገንዘብ ወይም የሌላ ጥቅማ ጥቅም ተገዢ መሆን የለበትም። አገልጋዩ ጥቅም ፈላጊ አለመሆኑን ከተመለከቱ ሕዝቡ የሚናገረውንም ቃል በአክብሮት ይሰሙታል።

እዚህ ላይ ጴጥሮስ «መጥፎውን ረብ በመመኘት» ሲል የግድ ገንዘብን ብቻ ማለቱ አይደለም። ቃሉ ታዋቂነትንና ዝነኛ የመሆን ፍላጐትንም ያካትታል፤ እነዚህ ነገሮች በሰው ጥልቅ ልብ ውስጥ ያሉ አደገኛ ፈተናዎች ናቸው። አንዳንድ ጊዜ ታዋቂ መሆንንና ዝነኝነትን ከገንዘብ አስበልጠን እንመኛለን።

«ገንዘብን ከመውደድ ወይም ዝነኛና ታዋቂ ከመሆን የትኛው የከፋ ሊሆን እንደሚችል ለይቶ መናገሩ አስቸጋሪ ነው። አንዳንድ ጊዜ ሰባኪዎች በሕዝቡ ዘንድ ታዋቂና ተወዳጅ ለመሆን በማሰብ ስብከታቸውን ለሰዎች በሚጥም መልኩ ያቀርባሉ። ይህ ዝንባሌ ደግሞ በፍጹም ለአገልግሎት ብቃት እንዳይኖራቸው ያደርጋል። እንዲህ ያለው ዝንባሌ የአገልጋዩን ሕይወት ክፉኛ ከመጉዳቱም በላይ ሕዝቡንም አይጠቅምም»

ክርስቲያኑ መሪ ሕዝቡን በኃይል የሚገዛ አምባ ገነን መሆን የለበትም። «ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ» የሚለውም በዚህ ምክንያት ነው (5:3)። ታላቅ ወይም ዝነኛ መሆን የሚፈልግ መሪ ግን በትንሽ በትልቁ እየተነሣ ሕዝቡ ላይ መኩራራት ይጀምራል። የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ በፍጹም ትሕትና ነበር የተመላለሰው፤ እርሱን አገለግላለሁ ከሚል ሰው ደግሞ ከዚህ ያነሰ አይጠበቅም።

መንፈሳዊ መሪ በቃልም ይሁን በተግባር ምሳሌ መሆን አለበት። «ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ. . .» ይላል ጴጥሮስ (5:3)። አባባሉ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ከጻፈው ምክር ጋር ይስማማል፦ «በቃልና በኑሮ፤ በፍቅርም በእምነትም፤ በንጽሕናም ለሚያምኑቱ ሁሉ ምሳሌ ሁን» (1ኛ ጢሞ. 4:12)። መሪዎች ሕዝብን ማስተዳደር ያለባቸው በእውነተኛ አረኛ ልብ ወይም ዝንባሌ መሆን አለበት። *መግቡ* ወይም *ጠብቁ* የሚለው ቃል የአንድ መልካም ባለ አደራ የሥራ ድርሻን ያመለክታል። መንጋው ከእግዚአብሔር በኃላፊነት የተቀበሉት እንጂ የእነርሱ ንብረት አይደለም፤ በመጨረሻም ተጠያቂነታቸው ለእርሱ ይሆናል። እግዚአብሔር የእረኞች አለቃ ነው፤ እነርሱ ደግሞ ከእርሱ በታች ያሉ እረኞች ናቸው።

የሚመሩት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እስከሆነ ድረስ አገልግሎታቸው ለሕዝቡ መጸለይና መማለድንም ይጨምራል። አንድ በሕንድ አገር የነበሩ አገልጋይ በእርሳቸው ሰበካ ውስጥ ለነበሩ መሪዎች አንድ በአንድ ስማቸውን እየጠሩ ይጸልዩ ነበር፤ ከዚህም የተነሣ በሰላሳ ዓመት አገልግሎታቸው የአማኞች ቁጥር በሦስት እጥፍ ከማደጉም በላይ የእርሳቸው አገልግሎትም እጅግ ፍሬያማ ሆኖአል።

አገልጋይ ትሕትናን እንደ ልብስ የለበሰ፣ እንደ መቀነትም የታጠቀ መሆን አለበት። እዚህ ላይ ልብስ ወይም መቀነት ሲል በወቅቱ ባሪያዎች ጌቶቻቸውን ሲያገለግሉ የሚታጠቁትን ወይም የሚያሸርጡትን ነጭ ልብስ ያመለክታል። መንፈሳዊ መሪ የአገልጋይ ሽርጥ መታጠቅ አለበት። ጴጥሮስ ይህን ሲጽፍ ጌታ ያደቀ መዛሙርቱን እግር ባጠበበት በዚያ ምሽት ታጥቆት የነበረውን ማበሻ እያስታወሰ ሳይሆን እንዳልቀረ አስባለሁ። ጌታ ይህን ያደረገው ትሕትናን ሊያስተምራቸው ነበር፤ ጴጥሮስ ግን በወቅቱ የትሕትናን አስፈላጊነት ስላልተረዳ «በፍጹም፣ አንተ የእኔን እግር አታጥብም» በማለት አንገራግሮ ነበር። ስለሆነም እርሱ የፈጸመውን ስሕተት እነርሱ እንዳይፈጽሙ ይመክራል። ምን ጊዜም ሥልጣን ባለበት ስፍራ ትዕቢትም ይኖራል፤ እግዚአብሔር ደግሞ በትዕቢተኞች መገልገልን አይፈልግም። እርሱ ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤ ትሑት ልብ ላላቸው

ግን ጸጋውን ያበዛላቸዋል። አንድ አገልጋይ ከሌሎች ጋር ባለው ግንኙነት ትሑት መሆን እንደሚገባው ጴጥሮስ ቊጥር 5 ላይ ያመለክታል። ቊጥር 6 ላይ ግን የእግዚአብሔርን ተግሣጽ በምን ዓይነት መንፈስ መቀበል እንዳለባቸው ሲያመለክት «ከኃይለኛው ከእግዚአብሔር እጅ በታች ራሳችሁን አዋርዱ» ይላል።

በዚህ መልክ ቢያገለግሉ ስለሚቀበሉት ዋጋ ሲናገርም «የእረኞች አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብር አክሊል ትቀበላላችሁ» ይላል (5፡4)። አንድ አገልጋይ ይህን በማሰብ ማገልገል አለበት። እዚህ ላይ «የማያልፍ» የሚለውን ቃል «የማይጠወልግ፣ የማይደርቅና የማይረግፍ» በሚሉ ቃላት መተካት ይቻላል። በዚያ ዘመን ታላላቅ ሰዎች ከአበባና ከቅጠላ ቅጠል የተሠራ ጉንጉን ይሸለሙ ነበር፤ ያ አበባ ወይም ቅጠል ከጊዜ በኋላ ጠውልጐ ይረግፋል፤ እውነተኛ መሪዎች የሚቀበሉት ሽልማት ግን የማይደርቅና የማይጠወልግ ከቶውንም የማይጠፋ ነው።

አንድ እረኛ ወይም መንፈሳዊ መሪ የቱንም ያህል ሽክም ቢበዛበትም የእረኞች አለቃ ሽክሙን እንደሚጋራለት የተሰጠው ተስፋ ሊያበረታታው ይገባል። ስለዚህም ጭንቀት ወይም ስጋት አይኖርበትም። «እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት» የሚለው ተስፋ ቃል እውነተኛ ነው። መንፈሳዊ ሽክሙን ለእግዚአብሔር መስጠትን የዘወትር ልምዱ ማድረግ አለበት።